# ግብረሰዶማዊነት እና የሴቶች «ክህነት» በቤተ-ክርስቲያን ዕይታ

በቅዱስነታቸው ብፁዕ አቡነ ሺኖዳ ፫ኛ
የኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ

ትርጉም
በመ/ር ተስፋ እንዳለ
እና
በዲ/ን ማለደ ዋስይሁን
፲፱፻፺ ዓ.ም
አ.አ

ማውጫ ገጽ

## ክፍል አንድ

1. ግብረሰዶማዊነት
1.1. የቤተ-ክርስቲያን ቅድስና . . . . . . . . 8
1.2. ግብረሰዶማውያንና የተፈጥሮ ሕግ . . . . . . . . 12
1.3. ግብረሰዶማውያን እና መንግስተ ሰማያት . . . . . . . . 13
1.4. ግብረሰዶም ውጤቱ ምን ነበር . . . . . . . . 13
1.5. ግብረሰዶማውያን በዘመነ ሐዲስ . . . . . . . . 13
1.6. ግብረሰዶማዊነት እና ጤና . . . . . . . . 17
1.7. ግብረሰዶማዊነትና ወንድነት . . . . . . . . 17
1.8. ግብረሰዶማዊነትና የቤተክርስቲያን ክብር . . . . . . . . 18
1.9. ግብረሰዶማዊነት እና ምስጢራተ ቤተክርስቲያን . . . . . . . . 19
1.10. የግብረሰዶማውያን መብቶች . . . . . . . . 20
1.11. ግብረሰዶማውያን «ካህናት» . . . . . . . . 20
1.12. ግብረሰዶማዊነትና ፍቅር . . . . . . . . 21
1.13. ግብረሰዶማዊነት በሰው ባሕርይ . . . . . . . . 22
1.14. ሌሎችን የምናስደስትባቸው መንፈሳዊ መንገዶች . . . . . . . . 23
1.15. የንስሐ መንገድ . . . . . . . . 25
1.16. የካህናት ሥልጣን . . . . . . . . 25
1.17. የካህናት ከባድ ኃላፊነት . . . . . . . . 27
1.18. ጥያቄዎች . . . . . . . . 28
ሀ. የተከፋፈለች ቤተ-ክርስቲያን እንዴት አንድ ትባላለች? . . .
ለ. ባልንጀሮቻችንን ሳንጎዳ በስምምነት ሥጋዊ ደስታን ማድረግ አንችልም? . . . . . . . .
ሐ. ግብረሰዶማውያንን እንዴት ልንረዳቸው ልናቀርባ[illegible]ውስ እንችላለን? . . . . . . . .

ገጽ

መ. በባልና ሚስት መካከል ያለ የግንኙነት ፍላጐት ተገቢ መሻት ወይስ የሽንፈት ጫና? . . . . . . . . . . . . .
ሠ. ምዕመናን ቅዱሳን ከተባሉ ጌታ እስከመከር ይኑሩ ያላቸው እንክርዳዶች ወዴት ናቸው?. . . . . . . . . . . . . . .
ረ. የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚሳተፉ ግን የተለያዩ የሚባሉ አካላት አሉ? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
ሰ. ከተግባሩ በንስሐ የተቆጠበ በውስጡ ግን ፍላጐት የሚታገለው ግብረሰዶማዊ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ይታያል? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
ሸ. የግብጽ ቤተ-ክርስቲያን ስለሰው ሰራሽ የእርግዝና መከላከያ ያላት አስተያየት ምንድነው? . . . . . . . . . . . .

## ክፍል ሁለት

2. የሴቶች «ክህነት» . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 37
2.1. የመጽሐፍ ቅዱስ ክብር . . . . . . . . . . . . . . . . 37
2.2. ሴቶች በኮፕቲክ ቤተክርስቲያን . . . . . . . . . . . . 40
2.3. ሴቶች በመጽሐፍ ቅዱስ . . . . . . . . . . . . . . 41
2.4. ክህነት በመጽሐፍ ቅዱስ . . . . . . . . . . . . . . 42
2.5. ክህነት በቤተክርስቲያን ትውፊት. . . . . . . . . . . 43
2.6. ድንግል ማርያም እና ክህነት . . . . . . . . . . . . 45
2.7. ዲያቆናዊት እና የምስዋዑ አገልግሎት . . . . . . . . 46
2.8. ሴቶች እና የክህነት ሥራ . . . . . . . . . . . . . . 47
2.9. የቤተክርስቲያን የምስጢራት አገልግሎት የተሰጠው ለማን ነው?. . . . . . . . . . . . . . . . . 48
2.10 የሴቶች ኃላፊነቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . 50

ገጽ

2.11 ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 51
ሀ. ሴቶችን ክህነት የሚሾም ጳጳስ በቤተክርስቲያን የሚኖርበት ሁኔታ እንዴት ነው? . . . . . . . . . . . . . .
ለ. የሴቶች ክህነት እንዲቋቋም የዓለም አብያተክርስቲያናት ሲኖዶስ ይስማማል? . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
ሐ. በተወሰነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ትክክለኛነት ላይ ጥያቄ ለሚያነሱ የሚሰጡት ምላሽ ምንድን ነው? . . . .
መ. የክርስቶስን ሥጋና ደም በእጅ መውሰድ ለሴቶች ካልተፈቀደ ድንግል ማርያም በእጆቿ መያዝዋስ? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
ሠ. ቅዱስ ጳውሎስ «ሴት ስለወንድ ተፈጠረች እንጂ ወንድ ስለሴት አልተፈጠረም» ያለው እንዴት ይብራራል? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
ረ. ክርስቲያኖች ሁሉ ካህናት ናቸው የሚል ነገር አለ? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
ሰ. አንዳንድ አብያተክርስቲያናት ዕድሜያቸው ከ፲፫ ዓመት በታች ለሆኑ የክርስቲያን ልጆች ቁርባን አይሰጥም የሚሉት ለምንድን ነው? . . . . . . . . . . . .
3. ቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ማን ናቸው? . . . . . . . . . . . . . . 58

## መግቢያ

ጥንት ተብሎ ነበር ታሪኩ የተነገረን፡፡ መጽሐፍ ቅድስም በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰዎች ልዩ መገለጫቸውና መጥፊያቸው እንደነበር ያስነብበናል፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን አመቻችቶ ሳለ ሰው ግን ወደዚህ ድርጊት ለመግባት ለምን ይሆን የሚፈቅድ? «የተመሳሳይ ጾታ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው»፡፡ በተመሳሳይ ጾታ (ወንድና ወንድ ወይም ሴትና ሴት) መካከል ተፈጥሮአዊ በሆነ መሳሳብን ፈጣሪ አላኖረም፡፡ ያ ቢሆን ኖሮ ሔዋን የምትመች ረዳት ተብላ ባልተፈጠረችም ነበር፡፡ አስቀድሞ አዳም ገና ለምትፈጠረዋና በአምላክ ፈቃድ ውስጥ ላለችው ሔዋን የሚመች ረዳት ተደርጐ ተደርጐ ተፈጥሮአልና፡፡ ሌሎች በሕይወተ ሥጋ የሚኖሩ ፍጥረታት በሙሉ ከወንድነትና ከሴትነት ፆታ ወጭ አይደሉም፡፡ በእነዚህ ሁለት ፆታዎች በዘር የሚራቡ ፍጥረታት በሙሉ ተገድበዋል፡፡ የሰዶም ሰዎች ይህን ተፈጥሮአዊ ወሰን ነበር ያፈረሱት፡፡

በርግጥ ሰው በኃጢአት ሲሰለጥን እና ጸጋ እግዘአብሔር ሲርቀው ሕሊናው ስለሚቆሽሽ ድርጊቱን ለመመዘን ይቸገራል፡፡ ኃጢአቱ ጽድቅ፣ ጽድቁ ኃጢአት ይሆንበታል፡፡ አሁን ያለንበት ዘመን ስልጣኔ የመጠቀበት ዓለምን አንድ መንደር የማድረግ ክነዋኔ የተፋጠነበት ወንጌል በክርስቲያንም በአሕዛብም ቤት እየተሰበከ ያለበት ነው፡፡

ሆኖም ግን ሰዎች በተፈጠሮ የታደሉትን ነጻ ፈቃድ መቃወም ከጀመሩ ሰነበተ፡፡ በአውሮፓ፣ በአሜሪካና እንዲሁም በእስያ ግብረሰዶማውያን ሕጋዊ እውቅና እንዲሰጣቸውና ወንዶች ወንዶችን በባልነት፣ ሴቶች ሴቶችን በሚስትነት እንዲያገቡ ጠይቀው ፈቃድ ያገኙ ፈቃድ ለማግኘት በሂደት ላይ ያሉና ጠንከር ያለ ተቃውሞ የገጠማቸው በርካታዎች ናቸው፡፡ በሌላ መልኩ አንዳንድ የዓለማችን ክፍሎችም ልጆችን ከዐስር ዓመታቸው ጀምረው በት/ቤት ውስጥ የግብረሰዶማዊነት ትምህርት በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ እንግዲህ ግብረሰዶማዊነት መንግሥታትን፣ ድርጅቶችን፣ የሃይማኖት ተቋማትን ዜጐችን በመፈታተን ላይ ያለ ነው፡፡

የአንግሊካን «ቤተክርስቲያንም» የግብረሰዶም አራማጆችን ተቀብላ ካህናት እንዲሆኑ ፈቅዳለች፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የአንግሊካን ቤተክርስቲያን ተከታይ ሴቶች «ወንዶች በሴቶች ተፈጥሮአዊ ግብር የሚገቡና ለሃይማኖት አገልግሎት መሾማቸው ትክክል ከሆነ እኛም ከወንዶች ሃይማኖታዊ የአገልግሎት ድርሻ መሳተፍ ይኖርብናል በሚል ፅንሰ ሐሳብ ክህነት እንዲሰጣቸው ጠየቁ» የአንግሊካን ቤተክርስቲያን መሪዎችም ግብረሰዶማዊያን ካህናትን ከግብራቸው እንዲለዩ እራሳቸውን እንዲያነጹና እንዲቀደሱ ከማድረግ ይልቅ ሴቶችን ክህነት መሾም ቀለላቸው፡፡ እነዚህን ሁለት ጉዳዮች አስመልክቶ የግብፅ ፓትሪያርክ አቡነ ሺኖዳ ጠለቅ ያለና ለትውልድ ሁሉ የሚበጅ እውነትን የያዘ ትምህርት ሰጥተዋል፡፡ ጉዳዮችንም በተመለከተ ለቀረቡላቸው ቃለ-መጠይቆች የክርስትና ትምህርትን መሠረት ባደረገ መልኩ መልሰዋል፡፡

በክፍል አንድ ትምህርታቸው የግብረሰዶምን ምንነት፣ የግብረሰዶማውያንን ሃይማኖታዊ፣ ስነምግባራዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊ እና ሰብአዊ ዕጣ ፈንታን የሚገልጽ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በክፍል ሁለት ትምህርታቸው ስለ ክህነት እና ወንዶችና ሴቶች በክህነት አገልግሎት ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የግብፅ ቤተክርስቲያን በስነተዋልዶ ትምህርት ላይ ያላትን አቋም አብራርተዋል፡፡ እኛም ትምህርታቸው ለኢትዮጵያውያን ምእመናን የሚያንጽ በመሆኑ ተርጉመን ለማቅረብ እና በዚያውም የቅዱስነታቸውን ማንነት በጉልህ ለመረዳት ለሚፈልጉ የትምህርታቸው ምርኮኞች የሕይወት ታሪካቸውን የሚገለጽ አጭር ጽሁፍም አካተናል፡፡

በዚሁ አጋጣሚ ተርጉመን ለምእመናን እንድናቀርብ ያነሣሣንን መምህር መንግሥተአብ እያመሰገንን መጽሐፉ ለአንባቢያን ከጥፋት ማዳኛ እንደሚሆን እምነታችን ነው፡፡

## ክፍል 1

### 1. ግብረሰዶማዊነት

### 1.1 *የቤተ-ክርስቲያን ቅድስና*

የቤተ-ክርስቲያንን አቋም በማጽናት የሚታወቁት ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንቱ ሊቃውንት በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ የሚገኘውን *«ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን እናምናለን»* የሚለውን ምስክርነት ሰጥተዋል:: እኛም አዘውትረን እንላለን ቅድስት ቤተክርስቲያን ሐዋርያዊትና ዓለማቀፋዊት ናት:: ስለቅድስናዋም ለመናገር መነሻችን በዘመነ ሐዋርያት የነበረችው ቅድስናዋ የተመሠከረላት ቤተክርስቲያን ናት:: በዚያ ዘመን ሁሉም አማኞች ቅዱሳን ተብለው ይጠሩ ነበር:: በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቅዱስ ማለት የሚያምን ማለት ነው:: የምናምን ሁሉ ቅዱሳን ተብለን እንድንጠራ እድል የተሰጠን በእምነት፣ በጥምቀት፣ በቁርባን እና በልባችን ውስጥ በሚያድር መንፈስ ቅዱስ በመለየታችን ነው:: ክርስቲያኖች እንዲሁ ሰዎች ብቻ አይደለንም:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው የመጀመሪያው መልእክት ላይ እንደገለጸው ክርስቲያኖች የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እና ቤተ-መቅደሱ ነን:: ቤተ-መቅደሱ በመሆናችንም ከመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ጋር የሚሆን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ እና ደም በውስጣችን ያለን ልንሆን ይገባል:: በአማኞች የሚታይ መልካም ሥራም በቀላሉ ያከናወነው የየራሣችን ሥራ አይደለም:: የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በመሆናችን በውስጣችን ያደረ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው እንጂ::

እንዲሁም ደግሞ እኛ የእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ነን:: የእግዚአብሔርን አርአያና መልክ ለዓለም እናንጸባርቃለን:: ዓለምም በእርግጥም ክርስቲያኖችን የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን



በሥራና በባሕሪያችን ያያል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮም ሰዎች በጻፈው መልእክቱ መግቢያ ላይ ስለክርስቲያኖች ቅድስና እንዲህ ይላል:: *«ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ . . . ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ . . . በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁት ሁሉ . . .»* ሮሜ ፩፥፩-፯ በሌላም መልእክቱ *«በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ-ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት የእርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየሥፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን የተጠሩት . . .»* በማለት ይጽፋል:: ፩ቆሮ ፩፥፪ በዚህም የክርስቲያኖች መጠራት የእግዚአብሔር በሆነው የቅድስና ኑሮ ለመሣተፍ መሆኑን ይመሰክራል:: አሁንም በድጋሚ ለቆሮንቶስ ሰዎች ቃሉን በማጠንከር *«በአካይያ አገር ሁሉ ከሚኖሩ ቅዱሳን ሁሉ ጋር በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ-ክርስቲያን . . .»* ይላል:: ፪ቆሮ ፩፥፩

ይህንን ክብር የሰጣቸው በሮምና በቆሮንቶስ ላሉ ምእመናን ብቻ ሳይሆን ቤተ-ክርስቲያን በተመሠረተችባቸው አህጉረ ስብከቶች ሁሉ መሆኑን መረዳት ይገባናል:: በኤፌሶንና በፊልጵስዩስ ላሉ ክርስቲያኖችም መልእክትን ሲጽፍ በዚያ ለሚገኙ ሁሉም ቅዱሳን /ክርስቲያኖች/ ሰላምታ አቅርቧል:: ለዕብራዊያንም ቢሆን በተመሣሣይ *«ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ . . .»* እያለ በመጥራት የክርስቲያን ወገኖችን ቅድስና መስክሯል:: ዕብ ፫፥፩:: በዚህም ቤተ-ክርስቲያን ቅድስት፣ ክርስቲያኖችም ቅዱሳን ተብለው እንደሚጠሩ እንረዳለን::

እንግዲህ እኛ ቅዱሳን የምንባል ከሆነ የበለጠ በሚጠቅም መንገድ እንዴት መኖር አለብን? ለዓለምስ ያንን ቅዱስ አርአያነትና ምሳሌነት እንዴት መግለጽ እንችላለን?

www.ethiopianorthodox.org

በዘመነ ሐዋርያት ማንኛውም ሰው ወደ ቤተ-ክርስቲያን እንዲገባ አይፈቀድለትም ነበር:: የሚገባቸው ብቻ በቤተ-ክርስቲያን የምስጢር አገልግሎቶችና የጌታችንን ሥጋ እና ደም በመቀበል ለመሣተፍ ይችሉ ነበር:: የተጠራንበትም ቅዱሱ ሕይወት ይህ ነው:: ምክንያቱም እኛ ከቅዱሱ አባት የተወለድን ነንና:: ልጆችም ለመባል ሥልጣን ተሰጥቶናል:: ቅዱስ ጴጥሮስም *«እንደሚታዘዙ ልጆች ባለማወቃችሁ አስቀድሞ የኖራችሁበትን ምኞት አትከተሉ፤ ነገሩ ግን እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ»* በማለት አስተምሯል:: ይህም አስቀድሞ በሕገ ኦሪት የእስራኤል ወገኖች እንዲመሩበት የተሰጠ ሕግ እንጂ አዲስ ነገር አይደለም:: ፩ጴጥ ፩፥፲፬-፲፮ ዘሌ ፲፩፥፵፬ ::

እንግዲህ ክርስቲያኖች ቅዱሳን ከተባሉ ቅዱሳን በሥጋ ምኞት አይኖሩም፤ በመንፈስ ፈቃድ ይመላለሳሉ እንጂ:: የተቀደሰ ሰው ሁለት ባሕርያት አሉት:: አንደኛው በነፍሱ ፈቃድ የሚመራ የሥጋው ባሕርይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በፈቃደ እግዚአብሔር የሚመራ የነፍሱ ባሕርይ ነው:: በዚህ መሠረት ላይ የሚጓዝ ሰው በእግዚአብሔር መንፈስ (ፈቃድ) ሁለንተናው እንዲመራ የወሰነ ሰው ነው:: የዚህን ሰው ሥጋ እና ነፍስ የእግዚአብሔር መንፈስ እየመራው ነውና በሥጋውም በነፍሱም ቅዱስ ነው:: በዚህም የእግዚአብሔርን አርአያና ምሳሌነት የሚያንጸባርቅ ይሆናል:: ቅዱስ ጳውሎስ ለሮም ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ስለነፍስና ሥጋ ካስተማረው ጥቂቱን እንደሚከተለው እንይ:: *«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢያትና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቶኛልና»* ካለ በኋላ *«እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፤ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ፤ ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፤ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና መገዛትም ተስኖታል»* በማለት ይገልጻል:: ሐዋርያው በዚህ መልእክቱ የክርስቲያኖች (ምእመናንና ካህናት) አኗኗር በዚህ መሠረት ላይ የቆመ፤ የተጠሩበትም ዋነኛ ምክንያት የቅዱሱን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሰውነታቸው በመፈጸም ቅዱሳን ተብለው እንዲጠሩ የፈጣሪያቸው ፈቃድ መሆኑን ያስጨብጣል:: አስከትሎም *«ክርስቶስ በእናንተ ወስጥ ቢሆን ሰውነታችሁ በኃጢያት ምክንያት የሞተ ነው:: መንፈሣችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው::»* እያለ ሰውነታችን ስለኃጢአት የማይኖር ስለጽድቅ ግን የበረታ እንዲሆን የክርስቲያን ወገኖችን ያሳስባል:: በዚህም ሳያበቃ *«እንግዲህ ወንድሞች ሆይ እዳ አለብን እንደ ሥጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለሥጋ አይደለም:: እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና::»* እያለ ክርስቲያኖች ስለፈቃደ ሥጋ በማሰብና በዚህም ሐሣብ ላይ በመራመድ የእግዚአብሔር ልጆች መባል እንዳለባቸው ያስተምራል:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጆች የምንሆነው፣ አርአያና ምሳሌነቱን የምናንጸባርቀው፣ ቅዱሳንም የምንባለው በመንፈስ ሆነን የሥጋ ፈቃዳችንን በመጨቆን ስንኖር ነው::

የቤተ-ክርስቲያን አኗኗር ይህ ከሆነ፤ እንግዲህ ከዚህ አንፃር ዛሬ በዓለም ላይ በጣም እየተስፋፋ ስለመጣው ወደፊትም መነጋገሪያ ሆኖ ሊቀጥል ስለሚችለው ፈተና እሱንም ለማሸነፍ የጌታችን ኃይልና ጸጋ ስለሚጠይቀው ጉዳይ እናንሣ:: ይህም የግብረ-ሰዶማዊነት ጉዳይ

ነው:: መነጋገሪያ ጉዳይ ሊሆን የሚገባው ባይሆንም ይህን ጉዳይ መነጋገሪያ አድርጌ በማንሣቴ እጅግ እያዘንኩ በአገልግሎቴ ተገድጄ ልመክር ግን እወዳለሁ::

### 1.2. ግብረ-ሰዶማዊነት እና የተፈጥሮ ሕግ

የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚፈቀደው በጋብቻ በተጣመሩ መካከል ሲሆን ጋብቻ ደግሞ የሚፈቀደው በአንድ ወንድ እና በአንዲት ሴት መካከል ብቻ ነው:: በመሆኑም ከዚህ ጥምረት ውጪ ስለሆነ ማንኛውም ጾታዊ ግንኙነት ሊገለጽ የሚችለው ከተለመደው ውጪ የሚፈጸም (ጤናማ ያልሆነ) የተፈጥሮ ሥርዓትን የሚቃረን መሆኑን ነው::

በቅዱስ ማቴዎስና በቅዱስ ማርቆስ ወንጌል ላይ እንደተጻፈው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለግብረሰዶማዊነት ከጸሐፍትና ፈሪሳውያን ጋር ሲነጋገር እንዲህ ብሏል «ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው . . .» ማቴ ፲፱፥፬ ይህ ከሥነ-ፍጥረት ጀምሮ የነበረ ተገቢው የተፈጥሮ ሕግና የጌታችንም ፈቃድ ነው:: ከዚህ ቀድሞም ከተሠራ የተፈጥሮ ሥርዓት ውጪ የሄዱ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ሰዎች በሥጋ ፈቃድ ሲኖሩ ከእግዚአብሔር ከባድ ቅጣትን ተቀብለዋል:: በኖህ ዘመን የነበሩ ሰዎች አካሄድ በዚህ ጉዳና ስለነበር ንጹህ የነበሩ ስምንት ነፍሣት ኖህ ባዘጋጀው መርከብ ሲድኑ ሌሎች ግን በውኃ ጠፍተዋል:: እንዲሁም ደግሞ ይህን የርኩሰትን ሥራ ይሠሩ የነበሩ የሰዶም ሰዎች በእሣት ተቃጥለው ጠፍተዋል:: የዚህ ምክንያቱ ይህን የተፈጥሮ ሕግ በጣሰ መንገድ ኑሮአቸው ሁሉ በሥጋ ፈቃድ የተሞላና በነፍሳቸውም የረከሱ ስለነበሩ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

### 1.3. ግብረሰዶማውያንና መንግስተ ሰማያት

የሥጋ ሰዎች (ሥጋውያን) መንግስተ ሰማያትን ሊወርሱ አይችሉም:: ቅዱስ ዮሐንስ በራእዩ ስለሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም በተናገረበት ምዕራፍ እንዲህ የሚል እናነባለን:: «ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኩሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርሷ ከቶ አይገባም» ራዕ ፳፩፥፳፯::

### 1.4. ግብረሰዶማውያን በሞት ይቀጡ ነበር

በብሉይ ኪዳን ዘመን ግብረሰዶማዊነት በሞት የሚያስቀጣ ጸያፍ ነገር እንደሆነ እናነባለን:: በኦሪት ዘሌዋውያን መጽሐፍ ወስጥ እንዲህ የሚል ተጽፏል:: «ከሴት ጋር እንደምትተኛ ከወንድ ጋር አትተኛ ጸያፍ ነገር ነውና::» ዘሌ ፲፰፥፳፪ በዚህ መጽሐፍ በሌላ ምዕራፍ «ማናቸውም ሰው ከሴት ጋር እንደሚተኛ ከወንድ ጋር ቢተኛ ሁለቱ ጸያፍ ነገር አድርገዋልና፣ ፈጽመው ይገደሉ:: ደማቸው በላያቸው ነው::» በማለት የሚጠብቃቸውን ጽኑ ፍርድ ያመለክታል:: ዘሌ ፳፥፲፫

### 1.5. ግብረሰዶማዊነት በሐዲስ ኪዳንም የተወገዘ ነው

ሐዲስ ኪዳን ስለንጽሕና ሕግ እና ትምህርት ከብሉይ ኪዳን በምንም የሚያንስ አይደለም:: በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ግብረ-ሰዶማዊነትን በማውገዝ የተነገሩ አራት መልእክቶችን እናገኛለን::

1. ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ በመጀመሪያው ምዕራፍ «እውነትን በዐመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዐመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣልና» በማለት ይመሰክራል:: የእግዚአብሔር ቁጣ ለምን ተገለጸ? ዝቅ ብሎ

ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል «ስለዚህ እርስበእርሳቸው ሥጋቸውን ሲያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ እርኩሰት አሳልፎ ሰጣቸው» ሮሜ ፩፥፲፰፡፳፬ «አሳልፎ ሰጣቸው» ማለት ጸጋና ረደኤት መስጠቱን እንደነፈጋቸው ማመልከቱ ነው። ተላልፈውም የመሰጠታቸው ምክንያት ሥጋቸውን ሲያዋርዱ የራሣቸውን የርኩሰት ሥራ አያስተውሉም ነበርና ነው።

ይህን በመሰለም እብደት ሥጋቸውን ያረክሱ ነበር የሰውነታችን ክብሩ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ በመሆን የሚገለጽ ነው። ነገር ግን በጸያፍ ሥራ በርኩሰት ሥጋችንን የምናጠፋው ከሆነ ውርደት ነው፤ ክብራችን መንፈስ ቅዱስ ይርቀናልና። «ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘ ትን ትተው እርስ በእርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ። ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ።» ሮሜ ፩፥፳፮-፳፯ በሚለት ሐዋርያው የሚገልጸው የሰዶማውያን ዓይነት ጸያፍ ሥራ የእግዚአብሔርን ቁጣ ስለሚያፈጥን ነው። በዚህ መልእክቱም በግልጽ ይህ የሰዶማውያን ኃጢአት አእምሮን የሚያረክስና ያልተገባም በመሆኑ በዘመነ ሐዲስም የሚወገዝ መሆኑን ይጠቁማል። «ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ» በሚልበት ጊዜም ግብረሰዶማዊነት የተፈጥሮን ሥርዓት የሚቃረን መሆኑን በግልጽ ያስቀምጣል። በተጨማሪም ይህ የርኩሰት ሥራ ሥጋን ማዋረድ፣ ለቅጣትም ተላልፎ መሰጠት እንደሆነ ተናግሯል።

2\. ሌላውና ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በመጀመሪያ በጻፈውመልእክቱ ያስተላለፈው ትምህርት እንዲህ ይላል። «አትሳቱ፤



ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀራጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ (ግብረሰዶማውያን) የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም።» በዚህ ቃሉ የምንረዳው ይህን የመሰለ የሚፈጽሙ ሁሉ እግዚአበሔር ካዘጋጀው መንግስት ውጪ መሆናቸውን ነው። ፩ቆሮ፮፥፱

ደግሞም ፈቃደ ሥጋን ንቀው በመንፈስ ለሚኖሩ እንዲህ እያለ ያስተምራቸዋል። «ዝሙትን ሽሹ፤ ሰው የሚያደርገው ኃጢያት ሁሉ ከሥጋ ውጪ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢያትን ይሠራል።» በገዛ ስጋው ላይ ኃጢያትን ይሠራል የተባለውም የመንፈስ ቅዱስ ቤት በሆነ በራሱ ሰውነት ውስጥ የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና ነው። ሐዋርያው ከዚሁ ጋር አያይዞ «ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ-መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና የራሳችሁ አይደላችሁም» በማለት ስለማንነታችን በትኩረት ያስረዳናል። ስለዚህ የሰው ልጅ በገዛ አካሉ ላይ ኃጢያትን በሚሠራበት ጊዜ ራሱን ከመንፈስ ቅዱስ እየለየ ነው። ብርሀንና ጨለማ በህብረት (በአንድ ቦታ) መኖር (መገኘት) አይችሉምና። ቀድሞም እግዚአብሔር ብርሀንን ከጨለማ ለይቷልና። ዘፍ፩፥፫ ስለዚህ የሚያስነውር ሥራ በሰውነታችን በሠራን ጊዜ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ሊኖር (ሊያድርብን) አይችልም። «ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ» በማለት ሁለቱም (ሥጋና ነፍሳችን) የእግዚአብሔር ናቸውና በዚያም እርሱ መክበር እንዳለበት ቅዱስ ጳውሎስ ያስተምራል። በዚህ መልእክቱ በሌላው ምዕራፍ «የእግዚአብሔር ቤተ-መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታወቁምን? የእግዚአብሔር ቤተ-መቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ። እያለ ተመሳሳይ ትምህርት ይሰጣል።

ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ብቻ ሳያበቃ ለቆሮንቶስ ሰዎች *«ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆነ አታውቁምን እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም።»* ይላቸዋል። ፩ቆሮ ፮፥፲፮ ከዚህም የምንረዳው እኛ የክርስቶስ አካላት ሥጋና አጥንቱ መሆናችንን ነው። ሐዋርያው የዚህን ሐሣብ መሠረት ሲያስረዳን *«እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል . . .»* ገላ ፪፥፳ እንግዲህ ክርስቶስ በእኛ ውስጥ የሚኖር ከሆነ እንዴት በዚህ የርኩሰት ሥራ አካላችንን እናጠፋለን? እንዴትስ የመንፈስ ቅዱስን ቤትና የክርስቶስን አካል እናፈርሣለን? እንዴትስ በዚህ ዘግናኝ የኃጢያት ሥራ ውስጥ በመገኘት የእግዚአብሔርን አርአያና ምሳሌነት እናዋርዳለን? ይህም የቅድስና አኗኗርና የድንግልናን ሕይወት ፍፁም መቃወም ነው።

3\. ሐዋርያው ቅዱስ ይሁዳም በመልእክቱ *«እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራን በዙሪያቸው የነበሩ ከተማዎች በዘላለም እሳት እየተቃጡ ምሳሌ ሆነዋል።»* በማለት ባልተለመደና እጅግ አጸያፊ በሆነው የኃጢያት ሥራ ምክንያት ፈጥነው እንደጠፉ ይመሰክራል። ይሁዳ ፩፥፯

4\. ሌላው መልእክት ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በላከው በመጀመሪያ ክታቡ እንዲህ ይላል። *«ለበደለኞችና ለማይታዘዙ ለዐመፀኞችና ለኃጢያተኞች፣ ቅድስና ለሌላቸው፣ ለርኩሳን፣ አባትና እናትን ለሚገድሉ፣ ለነፍሰ ገዳዮችና ለሴሰኞች ከወንድ ጋርም ለሚተኙ /ሰዶማውያን/ በሰዎች ለሚነግዱ፣ ለውሸተኞችም በውሸት ለሚምሉ የብሩክ እግዚአብሔርንም ክብር እንደሚገልጥ ለእኔ አደራ እንደተሰጠኝ ወንጌልም የሆነውን ደህና ትምህርት ለሚቃወም ለሌላም ነገር ሁሉ ሕግ እንደተሠራ እንጂ ለጻድቅ እንዳልተሠራ ሲያውቅ ነው።»* ፩ ጢሞ ፩፥፱ በዚህ ቃሉ ቅዱስ ጳውሎስ ግብረ ሰዶማውያንን



ከነፍሰ ገዳዮች፣ ከርኩሳን፣ ከዐመፀኞች ጋር አንድ አድርጎ ፈርጇቸዋል።

በአጠቃላይ ከላይ በተነሡት የአራት መልእክታት ትምህርት የምንረዳው ይህ ከባድ የኃጢያት ሥራ በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ የተወገዘ መሆኑን ነው። እንዲህ ከሆነ ታዲያ በዚህ የኃጢያት ፍቅር ውስጥ ያሉትን ለማስደሰት እግዚአብሔርን ማሳዘን ይገባል? ቅድስናቸውን እንዳጡ ከመተውና በዘላለም እሳት እንዲቃጠሉ ከማበረታታት የመንገዱን ቀኝ ማሳየት አይሻልምን? ወይስ ለኃጢያት ሥራቸው ምክንያት እየሰጠን በቤተ-ክርስቲያን ስም ተግባራቸውን ሕጋዊ እናድርግ?

### *1.6 ግብረሰዶማዊነት የጤና ጠንቅ ነው*

በአሁን ጊዜ ጌታ እግዚአብሔር ኤድስን በሚያህል ክፉ ደዌ ዓለምን እያስጠነቀቀ ነው። ማስጠንቀቂያውም ሥጋቸውን ግብረሰዶማዊነትን ለመሰለ ርኩሰት ለሰጡ ወገኖች ነው። ይሁን እንጂ ሰዎች ይህን ተጨባጭ ክፉ ደዌ እንኳን በሚያስገርም ሁኔታ እየፈሩ አይደለም።

### *1.7 ግብረሰዶማዊነት ተባዕታይነትን (ወንድነትን) የሚቃረን ነው*

ተፈጥሮአቸው ተቃራኒ በሆነ መንገድ በሴት ግብር የገቡ ወንዶችን እንዴት ወንዶች ልንላቸው እንችላለን? እንዲህ ያሉት ወንድነታቸውን የጠሉ ባሕርያቸውንም የጨቆኑ በመሆናቸው በምንም መንገድ ወንዶች እንደሆኑ ሊታሰቡ አይችልም።

## *1.8 ግብረሰዶማዊነት የቤተ-ክርስቲያንን መልካም ስም የሚያጎድፍ ነው*

ቤተ-ክርስቲያን ስላላት የከበረና ከፍ ያለ የሃይማኖት ሐሳብ ካነሳነው ጉዳይ አንፃር ምን ልንል እንችላለን? ክርስትና በባሕርዩ ማራኪ የሆነ የመንፈሳዊነት ሐሣብን የሚያስተምር ነው። ነገር ግን ዛሬ በቤተ-ክርስቲያን ስም ግብረሰዶማዊነት ስለመኖሩ፣ ስለግብረሰዶም ተገቢነትና የማይገባ በመሆኑ ላይ ክርክር ስለመኖሩ ሌሎች የሃይማኖት ድርጅቶች ሲሰሙ ስለክርስትና የመንፈሳዊነት አስተምህሮ ምን ያስባሉ?

የቤተ-ክርስቲያን ሕይወት ግን አስቀድመን እንዳየነው የቅድስና ሕይወት ነው። የቅድስና ሕይወት ያላቸው ሁሉ የቤተ-ክርስቲያን አካላት ናቸው የርኩሰትን ሥራ የሚሠሩ ግን የቤተ-ክርስቲያን አካል ሊሆኑ አይችሉም። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ላይም የተጠቀሰው ይኸው ነው። *«ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።»* የሐዋ ፪፥፵፯ ጌታ ወደ ቤተ-ክርስቲያን ጠርቶ ያከበራቸው የሚድኑትን እንደሆነ መግለጹ ቤተ-ክርስቲያን የቅዱሳን ጉባኤ፣ ቅድስናም የሞላባት መሆኑን ያሳያል። ታዲያ በክርስትና ስም የተደራጁ ኃይሎች ግብረሰዶማዊነትን ሕጋዊ ለማድረግ እየወሰዱት ያሉት እርምጃ በየትኛው የሃይማኖት ልቦና የታሰበ ይሆን?



## *1.9 ግብረ-ሰዶማዊነት ምስጢራተ ቤተ-ክርስቲያንን የሚቃረን ነው*

እንዲህ ዓይነት የርኩሰት ሥራ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ ከሆነ በክርስትና ውስጥ ስለሚኖር የሕይወት ተሐድሶ እና አገልግሎት ምን መናገር እንችላለን? አዲሱን የክርስቶስን የሕይወት ጸጋ ተቀበልን ማለትስ እንዴት ይቻላል? የንስሐ ሕይወትንስ?. . . ዳግም ስለመወለድስ? የእኛው አካል በሆኑ ወገኖች መካከል እንዲህ አይነት ርኩሰት የሠለጠነ ከሆነ ምን አይነቱን ዳግም ልደት ነው የተቀበልነው? ስለመዳናችንስ እንዴት መናገር እንችላለን? ምንስ ዓይነት ድኅነት ነው? ስለጥምቀትስ ምን አይነት ጥምቀት ነው? እንዲህ አይነቱ ርኩሰት በፊታችን ተጋርዶ ስለምንስ አይነት ቁርባን እና የምስጢራት አገልግሎት ነው የምንሰብከው?

ግብረሰዶማዊነት የጋብቻን ሥርዓትና ራስን መግዛትን ክፉኛ የሚቃረን ነው። በግብረሰዶማዊነት የሚሰቃዩ ሁሉ ሊያፍሩ ይገባል። ግብረሰዶማውያን ስለመንፈሳዊ ሕይወት በሚገባ የማያውቁ ከሆነ እንዲያምኑ በአግባቡ መረዳት አለባቸው። ነገር ግን አንድ ሰው የሚኖረውን የሀፍረት ስሜት ካላጣ በስተቀር በአደባባይ ግብረሰዶማዊ ለመሆንና ነኝም ብሎ ለማወጅ /ለመናገር/ የማይታሰብ ነው። ይህ ግን እየሆነ ነው። ከሁሉም በላይ ሊታመን የማይችለው ደግሞ እንዲህ ያሉት ሰዎች ተግባሮቻቸውን ለማጽናት እነርሱ ያላከበሩትን ሰብአዊ መብት እንዲከበር መጠየቃቸው ነው። ሰው ግብረሰዶማዊ ሲሆን ሰው የመሆኑን ክብር ራሱ ጥሏልና። እነርሱ በዚህ አባባላቸው ግን «ሰው ሁኑ አትበሉን» እያሉ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

## 1.10. የግብረ ሰዶማውያን መብቶች

ግብረሰዶማውያን ያላቸው መብት ምንድን ነው? ብቸኛ መብታቸው ሕይወታቸውን ወደ ንሰሓ የመምራት ነው። ነገር ግን የዚህ የርኩሰት ሥራ፣ ሥጋን የማዋረድና ጸያፍ የኃጢያት ተግባር ውስጥ ለመኖር *«ሰብአዊ መብት»* የሚሉትን መጠየቅ ሊታሰብ የማይችል ነው። በተጨማሪም ይህንኑ ሐሳባቸውን ላበረታቱና ላስከበሩ *«የቤተ-ክርስቲያን አካላት»* ክህነት እንዲሰጧቸውም ጠይቀዋል። ነገር ግን በዚህ ተግባራቸው ጸንተው እያሉ ለጥያቄዎቻቸው አዎንታዊ መልስ ሰጥቶ እርምጃ ውስጥ መግባት ከክርስትና መሠረታዊ የሃይማኖት ሐሣብ ውጭ ነው።

## 1.11. ግብረሰዶማዊ «ካህናት»

የቤተ-ክርስቲያን ምዕመናን ካህናቶቻቸው ግብረሰዶማውያን መሆናቸውን ሲያውቁ በፊታቸውም ምስጋና ይግባውና *«የክርስቶስን ሥጋና ደም ይዘን ተገኘን»* ሲሏቸው ምን ሊሉ ይችላሉ? ግብረሰዶማዊ *«ካህናትስ»* ወደ ንስሐ ሳይቀርቡ፣ ሳያምኑ ሕይወታቸው ሳይስተካከል ምእመናንን እንዴት ወደ ሕይወት ሊመሩ ይችላሉ? አንድ ካህንስ ራሱን በንስሐ ሕይወት ሳያድስ እንዴት ሌሎችን ወደ ንስሐ ሊያመጣ ይችላል? ራሱን መግዛት ሳይችል እንዴት ሌሎችን ራስን ወደመግዛት ሊያደርሳቸው ይችላል? ንጹሕና እውነት በሆነው በክርስትና የቅድስና ሕይወት ውበት ሳይደሰት ስለምን አይነት ቅድስና ሕይወት ሊሰብክ ይችላል? እርሱ ገደብ በሌለው ሥጋዊ አኗኗር ሕይወቱን እየመራ እንዴት ሌሎችን በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ እንዲኖሩ ሊያሳይ ይችላል? ይህን የሚያደርግ ካህንስ ዘባች እንጂ አገልጋይስ እንዴት ይባላል?



## 1.12. ግብረ-ሰዶማዊነትና ፍቅር

በአሁን ጊዜ ግብረሰዶማዊነት በወንዶች መካከል ያለ ፍቅር እንደሆነ ቀለል ተደርጐ ይወሰዳል። ወንድሞች ሆይ በፍጹም ይህ ሊሆን አይችልም። ፍቅር መንፈሳዊና ንጹሕ ነው። ሌሎችንም በንጽሕና እንወዳለን። ሌሎችን የምንወድበት ፍቅር ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር የሚያጠፋ ሊሆን አይገባውም። ምክንያቱም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *«ከእኔ ይልቅ አባቱን፣ ልጁን፣ ሚስቱን እህቱን ወይም ወንድሙን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም።»* ብሏልና። ማቴ ፲፥፴፯ የበለጠ የምንወደው ሌላ አካል ሊኖር አይችልም። ያለን ማንኛውም ፍቅር በጌታ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ መሆን ይገባዋል። በጌታችን ፈቃድ እንወዳለን፤ ከፈቃዱ ውጪና በመቃረን የምንኖረው ፍቅር የለም።

ግብረሰዶማዊነት በሥጋ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ርኩሰት እንጂ ፍቅር አይደለም። በሥጋ ፍላጐት እና በፍቅር መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። እንዲህ ላለው የኃጢያት ግንኙነት ፍቅር የሚስማማው ቃል አይደለም። ምክንያቱም በወንጌል *«እግዚአብሔር ፍቅር ነው»* እንላለንና፤ ታዲያ በዚህ ተክተን *«ግብረሰዶማዊነት ፍቅር ነው»* ልንል እንዴት እንችላለን? ይህ መንፈሳዊና ንጹሕ የሆነው ፍቅር አካል አይደለም። የገዘፈ የሥጋ ፈቃድ፣ መታረምም ያለበት ፍትወት ነው እንጂ።

አንድ ወንድ ሌላውን ወንድ የሚወድ ከሆነ፣ የወደደውን ያጠፋዋልን? ይህ ፍቅር ነው ወይስ ማጥፋት? አንድ ወንድ ሌላውን የወደደው ከሆነ ዘላለማዊ ሕይወቱን ሊያጠፋው ይችላልን? ለዘለዓለም ቅጣትስ አሳልፎ ይሰጠዋልን? ነቢያትና ሐዋርያት ግብረሰዶም የዘለዓለም ሞት እንዲያመጣ ጽፈዋልና። የእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌነቱን እንዲያጣ ማድረግስ ፍቅር ነውን?

### *1.13. ግብረሰዶማዊነት በሰው ባሕርይ*

ሌላው ይህን የጥፋት ሥራ ለማበረታት የሚቀርበው ማቻቻያ ምክንያት፤ ግብረሰዶማውያን እንዲሆኑ ተደርገው እንደተወለዱ አድርጐ ለማሳመን የሚሰጠው ሐሣብ ነው:: አንድ ግብረሰዶማዊ በዚህ መንገድ (ይህን ጽኑ የርኩሰት ሥራ እንዲወድ ሆኖ) ተወልዶም ከሆነ እንዲፈወስ፣ እንዲነጻ ሕይወቱ እንዲስተካከል ለማድረግ መጣር፣ እንዲድንም መጸለይ፣ ወደ ንስሐ መምራት፣ በመንፈሳዊ ኃይልና በሕክምና እንዲድን ማድረግ ይኖረብናል:: ነገር ግን *«ይሁን ግዴለም የቤተ-ክርስቲያን አካል እንድትሆን የቤተ-ክርስቲያንን የድኅነት ምሥጢራት እንድትካፈል ተቀብለንሃል»* ልንለው አይገባም:: አንድም ሰው በባሕርዩ ግብረሰዶማዊ ነው ልንለው አንችልም:: ግብረሰዶማዊነት ሊታረም የሚገባውና የሚችል በሰውየው ሕይወት ያጋጠመ ብርቱ የኃጢያት ልምምድ መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል::

በቤተ-ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የክርስቶስን የጸጋውን ብርሀን ገንዘብ ከማድረጋቸው በፊት አመንዝራ የነበሩ ብዙ ቅዱሳን አሉን:: እነርሱ በንስሐ ሕይወት ተመልሰዋል፣ ታርመዋል:: ይህም ሆኖ ግብረ-ሰዶማውያን ግን አልነበሩም፣ አመንዝሮች እንጂ:: ግብረሰዶማዊነት የማመንዘር ኃጢአት ይሁን እንጂ ያልተለመደና እጅግ የሚያጸይፍ ነው:: በተለመደ የማመንዘር /የኃጢአት/ ኑሮ ውስጥ አልፈው ኋላ በንስሐ የቤተ-ክርስቲያን ከዋክብት ከሆኑት መካከል ቅዱስ አውግስጢኖስ፣ ሙሴ ጸሊም፣ ፔላጌያ እና ሌሎችም ሊጠቀሱ ይችላሉ:: በእግዚአብሔር ጸጋና ረድኤት በእግዚአብሔር ርሕራሔና ጥበቃ ሕይወታቸው ተስተካክሎ ለክብርና ለማእረግ በቅተዋል:: እኛ ግብረሰዶማውያን በመሆናችን ለውድቀት ስንዳረግ



ግብረሰዶማዊነትን እንደተገቢ የሥጋ ሥራ ልንቀበል አይገባም:: ይህን አደረግን ማለት አጸያፊ ሥራ እንዲሰለጥንብን ፈቀድን ማለት ነው:: በዚህ ተግባር ውስጥ ያለን ሰው በኃጢያቱ እንዲጸና (እንዲበረታ)፣ ንስሐን እንዳያስብ ፈቀድንለት ማለት ነው:: በተጨማሪም ግብረሰዶማውያን ካህን የመሆን መብት አላቸው ማለታችንም ነው::

### *1.14. ሌሎችን የማስደሰት መንፈሳዊ ሕይወት*

የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እየናቅን ሰዎችን ግን ልናከብር አንችልም:: ወደገላትያ ሰዎች ከተጻፈው የሐዋርያው መልእክት ውስጥ ያሉ ትምህርቶችን እንመልከት:: *«ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኛለሁን? ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም»* ገላ፩÷፲:: የእግዚአብሔርን ቃል በሚቃረን መንገድ ሰዎችን ለማስደሰት የምንሄድ ከሆነ የክርስቶስ ባሪያ ልሆን አልችልም:: በተገቢው መንገድ ሰዎችን ለማስደሰት የምሻ ከሆነ ግን ወደ ንስሐ ሕይወት ልመራቸው ዝግጁ ነኝ:: ይህ መንፈሳዊ የሆነው ሰዎችን የማስደሰት አካሄድ ነው:: የምንወዳቸው ሰዎች በኃጢያት ጸንተው እንዲኖሩ፣ እንዲጠፉም መተው፣ ማበረታታትም ግን በመንፈሳዊነት ቀመር ውስጥ የለም::

ለሰዎች የምንሰጣቸው ደስታ ውግዘትንና ፍርድ የሚያመጣባቸው ከሆነ የፈጠርንላቸው ደስታ ጥቅሙ (ዋጋው) የት ላይ ነው? በርኩሰት የሚኖሩ ሁሉ ወደ መንግስተ ሰማያት እንዲገቡ አይፈቀድምና:: በሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ጳውሎስና ይሁዳ ትምህርት ውስጥ እንደተገለጸው አመንዝሮችና ሰዶማውያን በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ውስጥ እድል ፈንታ፣ ጽዋ ተርታ የላቸውም::



www.ethiopianorthodox.org

በቅርብ ጊዜ አንድ ጳጳስ ተብሎ ሊጠራ የማይገባው ነገር ግን «*ጳጳስ ነኝ*» ባይ ግብረሰዶምን ለማስከበር ወይም ቢኖር ነፍስን እንደማይጐዳ ለማሳመን የጻፈውን መጽሐፍ አንብበናል:: ይህ ሰው መጽሐፉን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስና ትምህርቱን በመቃወም ይጀምራል፣ ግብረሰዶምን ለማንገስ ለሚፈልጉ የዚህ ሐዋርያ ትምህርትና ውግዘት አያራምድምና:: ይሁንና ሐዋርያትና ትምህርታቸውን በመንቀፍ ሰዎችን ማስደሰት .እንችላለን? እግዚአብሔር በራሱ ተአምራዊ መገለጽ የመረጠውን ለሕዝብ ሐዋርያ እንዲሆን የተጠራን ሰው በመቃወም ሰዎችን ማስደሰት ተቀባይነት አለው?

የጌታችንን እውነተኛ ቃል ለመናገርና ለመጻፍ ከተመረጡት ሰዎች መካከል እንድንቆጠር በዚህ ጉዳይ ላይ ያለውን የቤተ-ክርስቲያን ግልጽ አቋም እንመስክር:: ጌታ «*መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ . . . ምስክሮቼ ትሆናላችሁ*» እንዳለ በዚህ የግብረሰዶማዊነት የኃጢአት ሥራ ምክንያት ስለሚያገኘ ን ጥፋት የነገረንን ቃል በእውነት እንመስክር:: የሐዋ. ፩፥፰

ጌታ እነዚህ ዐመፀኞች ንስሐ ካልገቡ እንደሚጠፉ አበክሮ አስተምሯል:: ይህ የጌታ ፍርድ በቅዱስ ሉቃስ ወንጌል ላይ ሁለት ጊዜ ተደጋግሞ ተጽፏል:: «*እላችኋለሁ፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ . . . አይደለም፤ እላችኋለሁ፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ*» ሉቃ ፲፫፥፫፣፭ እንዲህ ከሆነ ታዲያ ጌታ «*ንስሐ ባትገቡ ትጠፋላችሁ*» ስላላቸው ስለእነዚህ ኃጥአን (ግብረሰዶማውያን) «*አይደለም እኛ ይቅርታን እናገኝላችኋለን፣ መታረቂያም አላችሁ*» ልንላቸው እንችላለን? «*ቤተ-ክርስቲያን ትወዳችኋለች፤ ይቅርታንም ትፈልግላችኋለች፤ ስለዚህ በኃጢአት ቆዩ አትጠፉም*» ልንላቸውስ እንችላለን? በዚህ ሰዎችን



ልናስደስት አልታዘዝንም:: ይህ የእኛ ሥልጣንና ችሎታም አይደለም:: በእርግጠኝነት ለመናገር ኃጢአትን ተገቢ የተፈቀደ ለማስመሰል ምክንያቶችን መደርደር ኃጥአንንም ለማስደሰት መትጋት ከተሰጠን ሥልጣንና አቅም ውጪ ነው::

## *1.15. የንስሐ ሕይወት*

በመጀመሪያ ደረጃ ማወቅ ያለብን ነገር ኃጢአት የሠራ ሰው በቅድሚያ ያፍራል፤ ይሰማዋል፤ ይጨነቃል:: በዚህም ምክንያት የርኩሰት ሥራውን በአንዴ ሊያምን ሊቀበልም አይችልም:: እኛ ደግሞ በኃጢአቱ ካበረታነው የበለጠ ይደፍራል:: በተለይ ይህ ሰው ግብረሰዶምን ከፈጸመ፤ በግልጽ ግብረሰዶማዊነቱን በአደባባይ ካወጀ፤ ንስሐን ከመሻት ይልቅ ሰዶማዊ ሆኖ ለመኖር የመብት ጥያቄ ማቅረብ ከጀመረ፤ ከዚያም አልፎ ካህን ለመሆን ከደፈረ ይህ በእውነት የጭካኔ ሥራ ነው፤ በራስ ላይ መጨከን::

ነገር ግን ለዚህ ሰው ሥራው ኃጢአት መሆኑን የእግዚአብሔርንም ፈቃድ እየተቃወመ መሆኑን ግልጽ ካደረግንለት ምናልባትም ህሊናው የራሱን ሥራ መቃወም ይጀምራል:: አዘውትሮም ራሱን ያወግዛል፤ ይወቅሳልም:: «*ንስሐ ልትገባ ይገባሀል፤ መንገድህን መለወጥ አለብህ*» በማለት ራሱን ይመክራል::

## *1.16. የካህናት ሥልጣን*

በቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል ተጽፎ እንደምናነበው «*እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል*» ማቴ ፲፰፥፲፰ በማለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ ሥልጣነ ክህነትን ሰጥቷቸዋል:: ይህም ያሰራችሁት ወይም

የፈታችሁት ማናቸውም ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የተስማማ፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በማክበር ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት ማለቱ ነው። ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በተቃረነ መንገድ የታሰረም ይሁን የተፈታ ምንም ነገር ተቀባይነት አይኖረውም። እንዴትስ ሊሆን ይችላል?

በገላቲያ ላሉ ምእመናን የተጻፈውን የሐዋርያውን መልእክት ስናነብ የተወሰኑ የሚያስፈሩ ቃላት እናገኛለን። *«ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን፤ አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን»* ገላ ፩÷፰-፱። እንደካህናት ስንኖርም ትልቁ የአገልግሎት ድርሻችን ቀድሞ በተሰበከልን ወንጌል፣ በእግዚአብሔር ትዕዛዛት ላይ ተመሥርተን መምራት ነው። የእግዚአብሔር ሕግጋትን በመቃረን የትኛውንም ጉዳይ በአዲስ መልክ የማወጅ ሥልጣን የለንም። እንዲህስ ከሆነ ጌታ ስለምን ሥልጣንን ሰጠን? የተሰጠን የማሰርና የመፍታት ሥልጣንስ እንዴት ይገለጻል? ሥልጣናችን ግብረ ሰዶምን ለመባረክ የተቸረ ነውን? በነቢዩ ሚልኪያስ የትንቢት ቃል ውስጥም እንዲህ የሚል ቃል ተጽፏል። *«ካህኑ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር መልእክተኛ ነውና ከንፈሮቹ ዕውቀትን ይጠብቁ ዘንድ ይገባቸዋል። ሰዎችም ሕግን ከአፉ ይፈልጉ ዘንድ ይገባቸዋል»* ሚል ፪÷፯ ። በመሆኑም ካህናት ሕግን ያስተምራሉ እንጂ ሕግን አይሽሩም። ሰዎችም የጌታን ሕግ የሚያገኙት (የሚሰሙት) ከካህናት አንደበት ነው። ምክንያቱም ስለእግዚአብሔር ቃል ካህኑ ከየትኛውም ምእመን የተሻለ ዕውቀት አለውና። ካህኑ መምህር ነው፣ መሪ ነው። በመሆኑም በተሻለ በተረዳው በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት ይሰራል፤ በዚያም ላይ ተመሥርቶ ይፈታል እንጂ በተቃርኖ ቆሞ ይህን ሥልጣን ሊጠቀምበት አይችልም። ቅዱስ ጳውሎስ *«እኛም ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ . . .»* እያለ በተናገረው ቃል ከቅዱሱ ፈጣሪ ትዕዛዝ መሠረት በወጣ ሌላ የፍጡር መሠረት ላይ እንዳንታነጽ አሳስቧል። ይህንኑ ቃል በማጠናከር ባስልዮስ ዘቂሳሪያ ወቀጸዶቂያ *« . . ቅዱስ ጳውሎስ መላእክትን ለመርገም ደፈረ (በቃ)»* በማለት ይህን ቃሉን ያጸናል። በዚህ ቃል መሠረትም በጽኑ የተወገዘ መጥፎ ኃጢአትን ጽድቅ ለማድረግ የሚሰለፍ ካህን ሁሉ የእርግማኑ ሰለባ ነው።

### *1.17. የካህናት ጥንቃቄ የተሞላበት ኃላፊነት*

በብሉይ ኪዳን ከእግዚአብሔር ለካህናት የተሰጠ አንድ ወሳኝ ትዕዛዝ አለ። ይህም በነቢዩ ሕዝቅኤል የትንቢት መጽሐፍ ሁለት ጊዜ ተደጋግሞ ተጽፎ የሚገኝ ነው። እግዚአብሔር በሕዝቅኤል በኩል እንዲህ ይለናል። *«የሰው ልጅ ሆይ ለእስራኤል ቤት ጠባቂ አድርጌሃለሁ ስለዚህ የአፌን ቃል ስማ ከእኔም ዘንድ አስጠንቅቃቸው፤ እኔ ኃጢአተኛውን በእርግጥ ትሞታለህ ባልሁት ጊዜ አንተም ባታስጠነቅቀው፡ ነፍሱም እንድትድን ከክፉ መንገዱ ይመለስ ዘንድ ለኃጢአተኛው አስጠንቅቀህ ባትነግረው፤ ያ ኃጢአተኛ በኃጢአት ይሞታል። ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ።»* ሕዝ ፫÷፲፯÷፲፱ ይህን ቃል በሕዝ ፴፫ ላይም እናገኘዋለን። ጌታም ለዚህ ጉዳይ የሰጠውን ትኩረት እንረዳለን።

ምናልባት እኛ *«እረኞች ነን በእነዚህ በሚጠፉ ኃጢአተኛ ሰዎች ደም የምንሰቃየው የምንጠየቀውስ እንዴት ነው?»* እንል ይሆናል። ነገር ግን ካህናት ምእመናን ወደ ኃጢአት ሲጓዙ *«ይህ ወደ ጥፋት የሚመራ መንገድ ነው»* በማለት ማስጠንቀቅ ይኖርብናል።

ይህንን ካደረግን ነጻነት ይኖረናል:: እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል *«ነገር ግን አንተ ኃጢአተኛውን ብታስጠነቅቅ እርሱም ከኃጢአቱና ከክፉ መንገዱ ባይመለስ፤ በኃጢአቱ ይሞታል፤ አንተ ግን ነፍስህን አድነሃል»* ሕዝ ፲፡፲፱። ይህንንም ማሳሰቢያና የውግዘት ቃል ማክበር መፍራትም አለብን:: የተሳሳቱ ወገኖችንም ማስጠንቀቅ መመለስ አለብን:: *«ይህ የሞት መንገድ ነው፤ እንደ ሥጋ ፈቃድ ከሄድክ ትሞታለህ የእግዚአብሔርንም ትዕዛዝ ጠብቅ»* በማለት በመንፈስ የሚኖሩትን ልጆቻችንን ወደ ንስሐ ሕይወት ልንመራቸው ይገባል:: እንዲነጹ ለማድረግ መምከር አለብን:: ግብረ ሰዶማውያንን ለኃጢአታቸው ምክንያት እየሰጡ ማበረታታት ሳይሆን እንዲነጹ፣ እንዲፈወሱ፣ እንዲድኑ ማድረግ አለብን:: የማይገባውን ማድረግ ለእነርሱም ለእኛም አይጠቅምም: እነርሱም ይጠፋሉ፤ ደማቸውም ከእኛ ይፈለጋል::

### *1.18 ጥያቄዎች*

ጥያቄ 1.

በጸሎተ ሃይማኖት *«ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያን እናምናለን»* እያልን እንደግማለን:: ነገር ግን ይህች ሐዋርያት የሰበሰቧት ቤተክርስቲያን ከተከፋፈለች እንዴት ቅድስት ልንላት እንችላለን? መለያየት እና ቅድስናስ እንዴት አብሮ ሊሄድ ይችላል?

*መልስ:-*

በእርግጥ ይህ የሚያሳዝን ነገር ነው:: ይህም በመሆኑ ቤተክርስቲያን በእምነት፣ በትምህርተ መለኮት እና ሌሎች መሠረታዊ የሃይማኖት ሐሳቦች አንድ እንድትሆን ብዙ ሙከራ እየተደረገ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

በግብጽ ቤተክርስቲያን በኩል ይኸው ጉዳይ ትኩረት ይሰጠዋል:: ጌታችን መለያየትን አይቀበልም:: በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ *«ኖላዊ ሔር»* ብለን በምንጠራው ምዕራፍ ላይ ጌታ ቤተክርስቲያን አንድ መንጋ እንድትሆን መፈለጉ፤ እረኛዋም አንድ ራሱ ክርስቶስ እንደሆነ ተመልክቷል:: ዮሐ ፲፡፮ በሌላም በኩል ጌታ *«ቅዱስ አባት ሆይ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው»* ዮሐ ፲፯፡፲፮ በማለት ለሐዋርያቱ አንድነት በጠቅላላም ለቤተክርስቲያን አንድነት የአባቱን ፈቃድ ሲጠይቅ እናያለን:: ምንም እንኳን መለያየት፣ መከፋፈል የቅድስና ጉዳይ ባይሆንም ከላይ በተጠቀሰው አግባብ ግን ቤተክርስቲያን አንድ እንድትሆን ጥረት እያደረግን ነው::

ጥያቄ 2.

በምንኖርበት ጊዜ ሌሎች ባልንጀሮቻችንን ሳንጎዳ ሥጋዊ ደስታን ማድረግ አንችልም?

*መልስ:-*

በጥያቄው በቀረበው ሐሳብ መሠረት የሥጋ ደስታ ማድረግ የሚቻለው በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ወይም በጋብቻ ውስጥ ብቻ እንጂ የተፈጥሮን ሕግ በሚፃረር፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በሚቃወም አግባብ በመሄድ አይደለም:: ሰው በጾም ወራት ራስን በመግዛት ነገር ግን በተወሰነ ጊዜ ምግብን እና የሚጣፍጠውን በመውሰድ ደስታን ሊያደርግ ይችላል:: ነገር ግን ነፍሱን በመጨቆን፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመናቅ፣ የተፈጥሮን ሕግ በማፍረስ፣ የልብ ንጽሕናን በማጉደፍ መሆን የለበትም:: ብዙ ደስታዎች

ተፈቅደውልናል፤ ነገር ግን ጤናማ ያልሆኑና ተቀባይነት የሌላቸው አይደሉም::

ጥያቄ 3.

በቅድስና ሕይወት ለመራመድ፣ ለመፈወስ ዝንባሌና ፍላጎት ያላቸውን ግብረሰዶማውያን እንዴት ወደ ቤተክርስቲያን ልናቀርባቸው እንችላለን? እንዴትስ ልንረዳቸው እንችላለን?

*መልስ፦*

አስቀድሞ መያዝ ያለበት ነጥብ ቤተክርስቲያን የእነርሱ የጥፋት መንገድ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ስለሚቃረን እንደተገቢ ነገር መቀበል አትችልም:: ተግባራቸውን ተገቢ ልማድ በማድረግ ልንቀበል፤ ለዚሁም ተግባር በዚሁ መንገድ እንደተወለደ አድርገን ልናቻችልላቸው አንችልም:: ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ኃጢአት ኃጢአት ነውና::

እነርሱን ለመርዳት የምንከተለው የመጀመሪያ መንገድ የሠሩትን «ይህ ኃጢአት ነው፤ ይህ ርኩሰት ነው» ብሎ በማሳመን ከዚህ የሥጋ ባርነት ተላቀው መንፈሳዊ ደስታን እንዲያደርጉ መምከር ነው:: የመንፈሳዊ ሕይወትን ጣዕም የቀመሰ ሰው ይህን የርኩሰት መንገድ ሊተው ይችላልና:: ምክንያቱም ሰዎች ዓለማዊ በሆኑ ጉዳዮች የተጠመዱ በመሆናቸው ለጸሎት፣ ለዝማሬ፣ ለመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ . . . ጊዜ አይሰጡም:: በዚህም ምክንያት መንፈሳቸው በጣም ይደክማል፤ ይህ የደከመ መንፈስ ደግሞ ፈተናን መቋቋም አይቻለውም:: በመንፈሳዊው መንገድ እንዲመላለሱ መንፈሳቸውን የምናጠናክረው ከሆነ ግን የተሻሉ (የታረሙ) ይሆናሉ::



እንዲሁም ደግሞ ስለእነርሱ በመጸለይ፣ በመጾም፣ በማስቀደስ እና በሌሎች ባሉን መንፈሳዊ መርጃ መንገዶች ሁሉ ልናግዛቸው ይገባል:: የሕክምና እርዳታ የሚያገኙበት ሁኔታም ካለ እንዲሞክሩ ማድረግ ያስፈልጋል:: ነገር ግን በየትኛውም መንገድ ኃጢአታቸውን ተገቢና ትክክለኛ ማድረግ አንችልም:: ምንም እንኳን እንደ ካህንና መምህር ብንመላለስ ይህን የማድረግ ሥልጣን ግን አልተሰጠንም::

ጥያቄ 4.

ቤተክርስቲያን በጋብቻ ውስጥና በባልና ሚስት መካከል ያለውን የግብረሥጋ ግንኙነት ፍላጎትን እንዴት ታየዋለች? ተገቢ መሻት ወይስ የሽንፈት ጫና?

መልስ፦

ቅዱስ አውግስጢኖስ «ተግባረ ሥጋ እንዲፈጸም የሚረዳው በተፈጥሮ ያለና የተሰጠ መሳሳብ ነው» ይለናል:: በመጀመሪያ ጋብቻ የሚያስፈልገው ልጆችን ለመውለድና እግዚአብሔር እስከፈቀደ የዓለም ኑሮ እንዲቀጥል ለማድረግ ነው:: ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ውስጥ ምንም መሻት (መሳሳብ) የሚፈጥር ነገር ባይኖር ሰዎች የግበረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት አይኖራቸውም:: በምግብ ሁኔታ ብናይ፤ ምግብ ባይጣፍጠንና የመብላት ፍላጎትም ቢጠፋ ሰዎች አይበሉም፤ ስለዚህም ይሞታሉ:: በመሆኑም ይህ ይሆን ዘንድ በእነዚህ ሥጋዊ ጉዳዮች የመሳሳብን ሁኔታ አኖረ::

ነገር ግን ስለግብረሥጋ ግንኙነት ስንናገር ጥቂቶች ለእግዚአብሔር ታላቅና ፍጹም ፍቅር ያላቸው ሰዎች ይህን ተግባር ፍጹም ወይም አዘወትረው ላይፈጽሙ ይችላሉ:: በሌላም በኩል ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው በመጀመሪያ መልእክቱ

እንዲህ ይላል *«ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር እርስበርሳችሁ አትከላከሉ:: ራሳችሁን ስላለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ»* አንድ ሰው ሲጾም ከምግብ በመወሰን ራሱን መግዛት እንዳለበት ይታወቃል:: በተመሳሳይ አንድ ሰው (ሚስት ወይም ባል) ነፍስን በሚጠቅም መንገድ ጾምንና ጸሎትን ማድረግ እንዲችሉ ለጊዜው ለመለየት መፍቀድ ወይም በጋራ መስማማት ይኖርባቸዋል:: ሁለቱም በጉዳዩ መስማማት አለባቸው:: ይህ ካልሆነ ግን አንዱ በሌላው ላይ ፈተናን መጥራት ይሆናል:: ይህም በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ነው ሊባል አይችልም::

ነገር ግን ሥጋችን የወደደውን ሁሉ እንዲፈጽምም መፍቀድ የለብንም:: ጠቢቡ ሰሎሞን የወደደውን ደስታ ሁሉ እንዳደረገ እንዲህ እያለ ይነግረናል *«ዓይኖቼ ከፈለጉት ሁሉ አልከለከልኳቸውም:: ልቤም በድካሜ ሁሉ ደስ ይለው ነበርና ልቤን ከደስታ ሁሉ አላራቅሁትም»* መክ ፪፥፲:: የዚህ ታላቅ ሰው ድምዳሜ ግን ምን ሆነ? የንጉሥ ሰሎሞን ሐሳብ ቀድሞ ካሰበው በተለየና በተቃራኒ ይቀርባል:: *«እጁ የሠራቻትን ሥራዬን ሁሉ የደከምሁበትንም ድካሜን ሁሉ ተመለከትሁ፤ እነሆ ሁሉ ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል ነበር:: ከፀሐይ በታችም ትርፍ አልነበረም»* ይለናልና:: መክ ፪፥፲፩ አንድ ሰው ከዓለሙ ሁሉ ደስታን ሊፈልግ ሊያደርግም ይችላል:: ውሎ አድሮ ግን ራስን የመግዛት ሐሳብ ሊያድርበት ይችላል::

ጥያቄ 5.

ሁሉም የቤተክርስቲያን አካላት ቅዱሳን ተብለው እንዲጠሩ ትኩረት የምናደርግ ከሆነ ጌታ ስንዴውና እንክርዳዱ እስከመከር አብረው እንዲኖሩ ከተናገረው ቃል ጋር እንዴት ማዛመድ እንችላለን?



*መልስ፦*

በእርግጥ እንክርዳዶች የቤተክርስቲያን አካላት አይደሉም:: ጌታችን ምሳሌውን ባብራራበት በማቴዎስ ወንጌል እንደተገለጸው እንክርዳዱ የዲያብሎስ ሥራ፣ ስንዴው ደግሞ የእግዚአብሔር ሥራ እንደሆነ እናያለን::

በዓለም የኃጢአት ሥራ አለ፤ ቅዱስ ሕይወትም (አኗኗር) አለ:: የእግዚአብሔር መንግስት (ጽድቅና ጸጋው) ግን ሁሉንም ዓለም ያጠቃልላል (ይይዛል) ማለት አንችልም:: ነገር ግን የቤተክርስቲያን አገልግሎት ብዙ ስንዴ እንዲኖራት የሚቻልም ከሆነ እንክርዳዱንም ስንዴ እንዲሆን የመምራት ተልዕኮ ይዛለች ማለት ይቻላል:: የሌሎችን ሕይወት ማስተካከል ሥራችን ነውና:: በርግጥ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእንክርዳድ መስሎ የተናገረው ስላልተመለሱትና ስለሚጠፉት ሰዎች ነው:: በዓለም ላይ የሚፈረድባቸው (እንክርዳዶች) እና የሚፈረድላቸው (ስንዴዎች) ቢኖሩም ቤተክርስቲያን ግን ዛሬ ላይ ሆና ስትናገር ያላት ስንዴ ብቻ መሆኑን ነው::

ቤተክርስቲያን የምትታወቀው እግዚአብሔርን በሕብረት የሚያመልክ የተቀደሰ መንጋ እንዳላት ሆና ነው:: እነዚህም መንፈስ ቅዱስ የሚሠራባቸው የተቀደሱ ማህደሮች ናቸው:: የቤተክርስቲያን ማለትም የእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የሆኑ የእግዚአብሔር እውነተኛ ልጆች የእርሱን አርኣያና ምሳሌነት የሚጠብቁ፣ በመንፈስ ቅዱስ አንድነት ያላቸው የተቀደሰ ሕይወትን የሚመሩ ሰዎች ሕብረት ነው:: እነዚህ የእውነተኛዋ ቤተክርስቲያን አካላት ናቸው:: እንክርዳዱ ግን የቅድስት ቤተክርስቲያን አካል አይደለም::

ጥያቄ ፮.

የእግዚአብሔርን እውነት በጋራ ስለሚሳተፉ ከአንድ መንጭተው ግን የተለያዩ ፣ ስለተለያዩም የማይረከሱ አካልት ልንናገር እንችላለን?

*መልሱ፦*

በእርግጥ ቅዱስና ርኩስን መለያየት ይኖርብናል:: ይሁን እንጂ የተለያዩ፣ ነገር ግን መልካም የሆኑ መንገዶች አሉ:: ለምሳሌ ጋብቻና የድንግልና ሕይወት ሁለት የተለያዩ መንገዶች ሲሆኑ የሚያደርሱት ግን ወደ አንዱ ፈጣሪ ወደ እግዚአብሔር ነው:: ነገር ግን ድንግልና እና ዝሙት ወደ ጌታ የሚወስዱ ሁለት የተለያዩ መንገዶች ናቸው ማለት አንችልም፤ አይደሉምም:: ከቅድስና ሕይወት ሳይወጣ በቅድስና ውስጥ ግን የተለያዩ የክብር መንገዶች ሊኖሩ ይችላሉ:: ይህም ተቀባይነት አለው::

በዚሁም ምክንያት በቅድስት ቤተክርስቲያን የተለያዩ ቅርንጫፎች ይኖራሉ:: ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ስለመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች ባስተማረው መረዳት ይቻላል:: እርሱም *«ጸጋ የተለያየ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው»* ይለናል:: በአንዲት ቤተክርስቲያን ውስጥ መምህራን፣ ካህናት፣ ነቢያት፣ ሌሎች ምእመናን ይኖራሉ:: እነዚህ ሁሉ በደረጃ (በማእረግ) ቢለያዩም ሁሉም ግን የተቀደሱ ናቸው:: በጥያቄው *«የእግዚአብሔርን እውነት በጋራ የሚሳተፉ»* እንደተባለው ከቅድስና ሕይወት ሳይወጡ፣ በዚያ ውስጥ ሆነው የሚሳተፉ ናቸው:: ጌታም መልካም ዘር ሠላሳ፣ ስልሳ፣ መቶ ያፈራል እንዲል:: መለያየት ቢኖርም መልካም ፍሬ ተብለዋል:: ነገር ግን በእሾህ የተከበበውና የደረቀው መልካም አልተባለም:: ወፎች የለቀሙትም እንደዚያው::



ጥያቄ 7.

አንድ ግብረሰዶማዊ ወደ ቤተክርስቲያን ቢሄድ፣ ንስሐም ቢገባ ከግብረሰዶማዊነት ተግባሩም ቢቆጠብ ነገር ግን የመሻት ሐሳቡ በውስጡ እየታገለው ቢሆን ይህ ሰው በእግዚአብሔር ዓይኖች እንዴት ይታያል?

*መልሱ፦*

አንዳንድ ጊዜ ንስሐ የተወሰኑ ደረጃዎች ይኖሩታል:: የመጀመሪያው ደረጃ ከኃጢአት ተግባር ራስን መከልከል ነው:: ምናልባትም በዚህ ደረጃ አንዳንዴ ከተግባሩ ብንታቀብም መሻቱ ግን ሊተናነቀን ይችላል:: በዚህ ደረጃ ላይ ተነሳሒው በሥጋ ቢነጻም በመንፈሱ ግን እንደቀረው እንረዳ::

ሁለተኛው ደረጃ ደግሞ አእምሮውን በመግዛት ፍላጎቱን ለመለወጥ የሚችልበት ነው:: ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ሐዋርያው *«እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሄ እለምናችኋለሁ:: እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው»* ሮሜ ፲፪÷፪ እንዲል:: ሰው አእምሮውን በመግዛት ግንዛቤውን ሊለውጥ ይችላል፤ የተለየ ሐሳብ ስለዓለም የተለየ የአስተሳሰብ መንገድ ያመጣል:: ኃጢአትን ደስታ ሳይሆን ርኩሰት እንደሆነች ያስተውላል:: አእምሮው በተለወጠ ጊዜ መሻቱም ይለወጣል::

ስለዚህ የመጀመሪያው ደረጃ ኃጢአት ማድረግን መተው ሲሆን ወደ ፍጹምነት የምንሻገረው ግን ኃጢአትን መጥላት ስንጀምር ነው:: ወደ ፍጹምነት እያደገ ላለ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ አጋዥነት



www.ethiopianorthodox.org

ለአዲሱ ባሕርዩው ኃጢአት የማይስማማው ይሆናል:: ታላቁ መምህራችን ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ የእግዚአብሔር ልጆች ኃጢአትን አያደርጉም ምክንያቱም የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና:: ባሕርያቸው ተለውጧልና ይለናል:: ይህም የሕይወት ተሃድሶን ያሳየናል:: ካህናትም እንደ እረኝነታችን ሥራችን በአዲሱ የሕይወት ሐሳባቸው ላይ እንዲያተኩሩ፣ መንፈሳዊ ሐሳባቸውንም በተግባር እንዲገልጹት ሰዎችን ወደዚህ የሕይወት ተሃድሶ (ንስሐ) መምራት ነው::

ዕለት በዕለትም ተነሳሕያን የሚቀበሉትን ብቻ ሳይሆን የሚስማማቸውን መንፈሳዊ ሕይወት ያገኛሉ:: በመንፈሳዊም ሕይወታቸው ውስጥ በእግዚአብሔር ደስታን ያገኛሉ::

ጥያቄ 8.

የግብጽ ቤተክርስቲያን በሰው ሠራሽ የእርግዝና መከላከያዎች ላይ ምን አስተያየት አላት?

*መልስ፡-*

የግብጽ ቤተክርስቲያን በማስወረድ(abortion) መንገድ ካልሆነ በስተቀር መከላከል ለሚፈልጉ መብት ትሰጣለች:: ይህም ማለት እርግዝናን ማቋረጥ /termination of pregnancy/ ሳይሆን መከላከልን /Prevention of pregnancy/ ብቻ ነው:: ትኩረት መደረግ ያለበት እርግዝና አንዴ ከተከሰተ ፅንስን ማስወረድ ኃጢአት ነው:: ሌላው ቀርቶ የፅንሱ ዕድሜ አንድ ሰዓት ብቻ ቢሆን እንኳን ማስወረድ ኃጢአት ነው:: ስለዚህም እርግዝናን በመከላከል ላይ ብቻ ያተኮረ ከሆነ ቤተክርስቲያኗ ትቀበላለች::



ክፍል 2.

## *2. የሴቶች «ክህነት»*

### *2.1 የመጽሐፍ ቅዱስ ክብር*

እኔ በመጀመሪያ ለእናንተ መናገር የምፈልገው እኛ ለመጽሐፍ ቅዱስ ያለንን ክብር ነው:: በእርግጥ ማንኛውም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚያከብር ምናልባት ይናገር ይሆናል:: ነገር ግን በተግባር የሁልጊዜ ጉዳዩ አይደለም::

ብዙ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ኃይለ-ቃል ከመተማመን (ከመመስረት) ይልቅ በራሳቸው አእምሮ፣ በማሰብ ችሎታቸው እና በራሣቸው መረዳት ላይ ይተማመናሉ::

እኛ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚለን ለማየት እና የትምህርተ መለኮታችን መሠረት፡ የዶግማችንም መነሻ ለማድረግ ዝግጁ ነን:: ለምሣሌም፡- መጽሐፈ ምሣሌን ብናነብ *«በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን በራስህም ማስተዋል አትደገፍ»* ይላል:: ምሳ ፫÷፭ ሰዎች በራሳቸው መረዳት ስለሚያዩ ብዙ ዶግማዎችና ብዙ የትምሕርተ መለኮት ፅንሰሐሳቦች እናገኛለን:: *«ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው»* የሚል ማስጠንቀቂያ በድጋሚ ተሰጥቷል:: ምሳ ፲፬÷፲፪ እንዲሁም ተመሣሣይ ጥቅስ በምሳ ፲፮÷፳፭ ተደግሟል::

ሰው የእርሱ አእምሮ /እውቀት/ ጥቅል እንደሆነ ሲያስብ የእርሱ የሥነ መለኮት መረዳት ለእርሱ ተስማሚ ይሆናል:: ይህ ምናልባት አንዳንድ ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚቃረን ትምህርት ነው:: ከራሣችን አእምሮ ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስን ማክበር ይገባናልና:: ይህ ከመጀመሪያ ጀምሮ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው::

ለምሳሌ ከሙሴ በኋላ እስራኤላዊያንን የመራውና የሙሴ ደቀመዝሙር ለነበረው ለኢያሱ የእኛ ጌታ እግዚአብሔር ምን እንዳለው ብናነብ *«የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው በዚያን ጊዜ መንገድህ ይቃናልሀል ይከናወንልሃልም»* ያለውን እናገኛለን:: ኢያ ፩÷፰

እንዲሁም ሙሴም እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት እንደሠራም ብዙ ጊዜ ተገልጿል:: በቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል ውስጥ በተራራው ስብከት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃሉ ላይ ምንም እንዳንጨምር ምንም እንዳንቀንስ አዝዞናል:: እንዲህ ለሚያደርግም ቅጣት ይሰጠዋል ብሏል:: ማቴ ፭÷፲፱::

እኔም መጀመሪያ ባቀረብኩት ትምህርቴ ከገላትያ መልእክት ላይ እንደጠቀስኩት ቅዱስ ጳውሎስ:- *«ነገር ግን እኛ ብንሆንም ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን የሚሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን»* ይላል ገላ ፩÷፰-፱:: እኛም መጽሐፍ ቅዱስንና የእርሱን ትምህርት ማክበር አለብን:: ይህንን የምልበት ምክንያት ጥቂት ምሑራን «የዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ዐስራ አንድ ምዕራፎች እና የነቢዩ ዮናስ ታሪክ እንዲሁም ጥቂቶቹ የነቢዩ ሕዝቅኤል ትንቢቶች አፈ ታሪኮች ናቸው» ማለታቸውን ስለሰማሁ ነው:: ሰዎች አእምሮአቸውን ለመጽሐፍ ቅዱስ በማስገዛት ፈንታ መጽሐፍ ቅዱስን ለአእምሮአቸው ማስገዛት ጀምረዋል:: እነርሱ የሚቀበሉት ሁሉ ትክክል ነው:: እነርሱ የሚቀበሉት ካልሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እነርሱ የማይቀበሉትን አያከብሩትም:: ስለሆነም እነርሱ ለመጽሐፍ ቅዱስ ያላቸው ክብር እንደሚገባው አይደለም::



አንዳንድ ሰዎች *«ይህ በብሉይ ኪዳን ስለተጻፈ አንቀበለውም እኛ የምንቀበለው በሐዲስ ኪዳን ወስጥ የተጻፈውን ብቻ ነው»* ይሉ ይሆናል! በብሉይ ኪዳን ወስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ቃል እንዴት እምቢ ማለት እንችላለን?

አንድ ጊዜ ከቤተክርስቲያን ባለስልጣን (ኦርቶዶክሳዊ ያልሆኑ) ጋር እየተወያየሁ ነበር:- እኔ ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ጥቅስ ጠቀስኩ:: እርሱ ግን *«ይህ በቅዱስ ጳውሎስ ተነገረ እንጂ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አይደለም»* አለኝ:: ከዚያ እኔም *«የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ከመንፈስ ቅዱስ ናቸው ወይስ አይደለም?»* ስል ጠየቅኹት እርሱም አሰበና *«አዎ ከመንፈስ ቅዱስ ናቸው»* አለኝ:: ታዲያ እኔም አሁን የጠቀስኩልህ *«እነኝህ በመንፈስ ቅዱስ የተነገሩ የእግዚአብሔር ቃላት ናቸው»* አልኩት:: እስቲ ለእኛ ጠቃሚ የሆኑ ሁለት ጥቅሶችን እናንብብ:: ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛው ጢሞቴዎስ መልእክት:- *«ከሕጻንነትህ ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍት አውቀሃል፤ የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል»* የሚል ጽፏል:: ፪ኛ ጢሞ ፫÷፲፭-፲፯ እንደገና ቅዱስ ጴጥሮስም:- *«ቅዱሳት መጻሕፍት በሰው ፈቃድ አልመጡምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩት»* ይላል ፪ኛ ጴጥ ፩÷፳፩::

ዶግማ እና ሥነመለኮት የትሕትናን መንፈስ ይፈልጋል:: ትሑት ሰው ራሱን ከቅዱሳት መጻሕፍት ባላይ ከፍ አድርጐ አያስቀምጥም:: መቀበል አለመቀበል፣ መጨመር ወይም መቀነስ ትሕትና አይደለም:: እኔ አስቀድሜ እንደተናገርኩ አንዳንድ ሰዎች

ቅዱሳት መጻሕፍት ግብረ ሰዶምን እንደሚቃወሙ ሲያውቁ ግብረ ሰዶማዊነትን ለማስከበር ቅዱሳት መጻሕፍትን ይቃወማሉ:: የሴቶች ክህነትንም ቅዱሳት መጻሕፍት እንደማይፈቅዱ ሲመለከቱ ሴቶችን ለማስደሰት የመጽሐፍ ቅዱስን ትምሕርት ለመቃወም ዝግጁ ይሆናሉ::

ስለዚህ እኔ የሴቶች «ክህነት» የሚለውን ትምህርት አሁን መመርመር እወዳለሁ:: በመጀመሪያ እንደ መግቢያ:- ሴቶች እናቶቻችን፣ እህቶቻችን እና ለእኛ መንፈሣዊ ልጆቻችን መሆናቸውን መናገር እፈልጋለሁ እኛ እነርሱን እንወዳቸዋለን፤ እናከብራቸዋለን:: ስለእነርሱም እንጸልይላቸዋለን:: በቤተክርስቲያን ወስጥም ኃላፊነቶችን እንሰጣቸዋለን::

## *2.2 ሴቶች በኮፕቲክ ቤተክርስቲያን*

በኮፕቲክ ቤተክርስቲያን በሺዎች የሚቆጠሩ ሴቶች የሰንበት ትምህርት ቤት መምህራን አሉን:: በካይሮ ብቻ ከዐስር እስከ ዐስራ አምስት ሺህ ሴቶች የሰ/ት/ቤት መምህራን አሉ:: በመንፈሣዊ ትምህርት ቤቶቻችንና በኮፕቲክ ተቋም የሚያስተምሩ አራት ሴቶች አሉን:: አንዷ ብሉይ ኪዳንን ታስተምራለች፤ ሁለተኛዋ የዕብራይስጥ ቋንቋ፤ ሁለቱ የቤተክርስቱያን ታሪክ ያስተምራሉ::

በማንኛውም ቤተክርስቲያን (በግብጽ ኦርቶዶክስ) የማኅበረሰብን እንቅስቃሴ የሚያደራጁና የሚከታተሉ (የሚቆጣጠሩ) ሴቶች አሉን:: በቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባዔ (መማክርት) ውስጥም ብዙ ሴቶች አሉን:: እነርሱም ብዙ ኃላፊነቶች አሉአቸው::



## *2.3 ሴቶች በመጽሐፍ ቅዱስ*

የሴቶች ኃላፊነቶች ለእነርሱ የተሰጡት ከመጀመሪያው ነበር:: ስለሆነም ብዙ ሴቶች ነቢያት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚገኙ መጥቀስ /መዘርዘር/ እንችላለን:: የሙሴ እህት ማርያም ነቢይት ነበረች፤ የእስራኤላውያን መስፍን የነበረችው ዲቦራ ነቢይት ነበረች:: እነርሱ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነበሩ:: ከጌታችን መስቀል አጠገብም አብዛኛዎቹ ሴቶች ነበሩ:: ከወንዶች ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ብቻ ነበር:: ሑልዳን ነቢይት ነበረች፤ በጌታችን ልደት ጊዜ የነበረችው የፋኑኤል ልጅ ሐና ነቢይት ነበረች:: ስለዚህም እነርሱ ነቢያት መሆን ይችላሉ፤ ችግርም የለውም:: ንግሥታትም ይሆናሉ፤ አስቴር ሁሉንም ሕዝብ ያዳነች ንግሥት ነበረች:: ይህ ትክክል ነው ብልህ /አስተዋይ ጥበበኛ/ ሴት ሕዝቦቿን ታድናለች:: ማርያም መግደላዊትም አስደሣቹን ዜና የጌታችንን ትንሣኤ ለአስራ አንዱ ሐዋርያት እንድታውጅ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶች ተልካ እንደነበር እናውቃለን:: ዮሐ ፬÷፲፯ በሐዋርያት ዘመንም ብዙ ሴቶች ቤቶቻቸው አብያተ ክርስቲያናት እንዲሆኑ ሰጥተዋል:: ከእነርሱ ውስጥም የወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ እናት ቅድስት ማርያም ነበረች:: ቤቷ ቤተክርስቲያን ሆነ:: ይህ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ወስጥ ተገልጾአል:: ሐዋ ፲፪÷፲፪ እንደገናም የአቂላ፣ የጵርስቅላ እና የልዲያ ቤትም በሮሜ መልእክት ውስጥ ተጠቅሶአል:: ሮሜ ፲፮

ብዙ ሴቶች ለጌታ ተልከዋል፤ እርሱንም አገልግለዋል:: ከነዚህም ጥቂቶቹ ሴቶች በቅዱስ ሉቃስ ወንጌል ተጠቅሰዋል «*ከዚህ በኋላ እየሰበከና ስለ እግዚአብሔር መንግስት የምሥራች እየተናገረ በየከተማይቱ በየመንደሩም ያልፍ ነበር:: ዐስራ ሁለቱም ከእርሱ ጋር ነበሩ ከክፉዎች መናፍስትና ከደዌም ተፈውሰው የነበሩ አንዳንድ ሴቶች እነርሱም:- ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት ማርያም*

*የምትባል፣ የሔሮድስ አዛዥ የኩዛ ሚስት፣ ዮሐናም፣ ሶስናም ብዙዎች ሌሎችም ሆነው በገንዘባቸው ያገለግሉ ነበር»* ሉቃ ፰÷፩-፫::

## *2.4 ክህነት በመጽሐፍ ቅዱስ*

ሴቶች ምናልባት ሙሉ ፍቅርና ትልቅ ስሜት ይኖራቸዋል:: ፍቅራቸውና ስሜታቸው ለክርስቶስ ታማኝ ከሆነ በጣም ጠቃሚዎች መሆን ይችላሉ:: ነገር ግን እንደዚህ ቢሆንም ሴት ካህን ሆና የሚያሣይ አንድ ነጠላ ምሳሌ እንኳ ከሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ ማግኘት አንችልም:: ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ሴቶችን እንደጨቆናቸው ሳይን ለሌላ ኃላፊነት እንደጠራቸው ያሳያል:: ክህነት መለኮታዊ ጥሪ ነውና:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሴቶች ለብዙ ብዙ ኃላፊነቶች እንደተጠሩ በእውነት ግልጽ ነው:: ለክህነት ግን አይደለም::

- የመጀመሪያው ክህነት የቤተክርስቲያን ፓትርያርኮች ክህነት ነው:: አባታችን አብርሃም፣ አባታችን ኖኅ፣ አባታችን ይስሐቅ፣ አባታችን ያዕቆብ እነዚህ ሁሉ ወንዶች ናቸው::
- ሁለተኛው የክህነት ዓይነት በዘፍጥረት ውስጥ የተገለጸው የመልከ ጼዴቅ ክህነት ነበር ዘፍ ፲፬፣ ዕብ ፯ እንዲሁም የአሮንና የልጆቹ ክህነት፤ ሁሉም ግን ወንዶች ነበሩ:: ዘጸ ፳፰÷፩

በአጠቃላይ በብሉይ ኪዳን ውስጥ አንዲትም ሴት ካህን አልነበረችም:: በትክክል እግዚአብሔር የፈለገው ቢሆን እርሱን ማን ይከለክለዋል? በሙሴ፤ አሮን እና ከአሮን ልጆች ለክህነት የሚመረጡትና ለእግዚአብሔር የሚቀደሱት የመጀመሪያ ልጆች ሁሉ ወንዶች ነበሩ::



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ ካህናት፣ ሊቃነ ካህናት ወይም የመጀመሪያ ዓለም አቀፋዊ ጳጳሳት እንዲሆኑ የመረጣቸው ዐስራ ሁለቱ ሐዋርያት ሁሉም ወንዶች ናቸው:: በእነርሱ የተሾሙትም የመጀመሪያዎቹም ጳጳሳት ወንዶች ናቸው::

## *2.5 ክህነት በቤተክርስቲያን ትውፊት*

በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ አይደለም፤ በትውፊት፣ በአጠቃላይ ታሪክ ወስጥም ምሳሌ የምትሆን አንድም ሴት ካህን አልነበረችም:: እኛ የመጽሐፍ ቅዱስን ዱካ እና ትምህርቱን መከተል አለብን:: ምክንያቱም የክርስቲያን ሕይወት ከአንድ ትውልድ ወደሚቀጥለው ትውልድ የሚቀባበሉት ነውና:: ለምሳሌ በመጀመሪያው የቆሮንቶስ መልእክት ቅዱስ ጳውሎስ ስለቅዱስ ቁርባን ሲናገር:- *«ለእናንተ ደግሞ አሣልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና»* ብሏል ፩ኛ ቆሮ ፲፩÷፳፫

እግዚአብሔር እምነትን (ዶግማን)፣ ሥነመለኮትን፣ ሥርዓተ ቅዳሴን ለሐዋርያት አሣልፎ ሰጥቶአቸዋል:: ሐዋርያትም ለደቀመዛሙርቶቻቸው (ለነርሱ ደቀመዛሙርት) ለመጀመሪያዎቹ ጳጳሳት አሣልፈው ሰጥተዋል:: እነርሱም ለሚቀጥለው /ለሌላው/ ትውልድ አሣልፈው ሰጥተዋል:: ይህ ዶግማ እስከ እኛም ጊዜ ደርሷል:: ስለዚህ ምክንያት ቅዱስ ጳውሎስ የኤፌሶን ጳጳስ ለነበረው ለደቀመዝሙሩ ጢሞቴዎስ *«ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎች ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ»* ብሏል:: ፪ኛ ጢሞ ፪÷፪

ትምህርቱ ከቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ፤ ከጢሞቴዎስ ደግሞ ለታመኑ ሰዎች እንደገናም ከነዚያ ከታመኑ ሰዎች ለሌሎች



www.ethiopianorthodox.org

ተሰጥቶ ነበር። ይህን ትውፊት ነው እስከ አሁን ድረስ በዘመናት ሁሉ ከሐዋርያት ጀምሮ የተቀበልነው።

በርግጥ እግዚአብሔር ሴቶችን ለክህነት መጥራት ቢፈልግ ሴቶችን ነቢያት እንዳደረገ ካህናትም ባደረጋቸው ነበር። ቤተክርስቲያን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ስብስብ ናትና።

እያንዳንዱ ተከታይ የተወሰነ ሥራ ያከናወናል /ይሠራል/ ሁሉም ተከታይ አንድ ዓይነት ሥራ መሥራት አለበት ማለት ግን አንችልም። በክርስቶስ ሰውነት እያንዳንዱ አባል የራሱ ማእረግ፣ የራሱ ክብር፣ የራሱ ሥራና የራሱ አስፈላጊነት /ጠቃሚነት/ አለው። ሁሉም ተከታይ ራስ፣ ሁሉም ዓይን ፣ ሁሉም እጅ፣ ሁሉም ልብ ይሆናል ማለት አንችልም።

ሴት ራስ ለመሆን ያልተጠራች ከሆነ ምናልባት ልብ ለመሆን ተጠርታ ይሆናል፤ ልዩነት ግን የለውም። እያንዳንዱ ተከታይ በቤተክርስቲያን ወስጥ የራሱ ሥራ አለው። ይህ ደግሞ ሐዋርያው ስለመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በተናገረ ጊዜ የተባለው ነው። እኛ የመጀመሪያው የቆሮንቶስ መልእክትን ስናነብ:- *«ዳሩ ግን አሁን ብልቶች ብዙዎች ናቸው፤ አካል ግን አንድ ነው . . . እግዚአብሔርም በቤተክርስቲያን አንዳንዶችን አስቀድሞ ሐዋርያት ሁለተኛም ነቢያት ሦስተኛ አስተማሪዎችን ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ እርዳታንም አገዛዝንም የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጕአል። ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን? ሁሉስ ነቢያት ናቸውን? ሁሉስ ተአምራትን ይሠራሉን? ሁሉስ የመፈወስ ስጦታ አላቸውን?»* ፩ኛ ቆሮ ፲፪÷፳

ነገር ግን እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ብልት የራሱን ሥራ ይሰጣል ወንዶችና ሴቶች በአንድ በተወሰነ ኃላፊነት ላይ ተፎካካሪ /ተቀናቃኝ/ መሆን ግን አይችሉም። ሴቶች ለቤተክርስቲያን ጠቃሚ



የሆነ ብዙ ሥራዎችን መሥራት ይችላሉ። ነገር ግን ለክህነት አልተጠሩም። በዚህ እኛ ተወቃሽ መሆን የለብንም። ምክንያቱም ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው እንጂ የእኛ አይደለም።

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን አንድ ምሣሌ መገኘት ከቻለ እኛ ልንቀበል ዝግጁ ነን። የእግዚአብሔርን ቃል እንቀበላለን እንጂ አንቃወምም። ነገር ግን አዲስ ትምህርት መጨመር ደግሞ አንችልም።

### *2.6 ራስ ማን ነው?*

ሐዲስ ኪዳን ራስ አድርጐ የሚጠራው ማንን ነው? ወንድን ወይስ ሴትን? ይህ በኤፌሶንና ቆሮንቶስ መልእክት ወስጥ *«ነገር ግን የወንድ ራስ ሁሉ ክርስቶስ የሴትም ራስ ወንድ ነው.......... ሴት ከወንድ ናት እንጂ ወንድ ከሴት አይደለም። ሴት ስለወንድ ተፈጠረች እንጅ ወንድ ስለሴት አልተፈጠረምና ስለዚህ ሴት ከመላእክት የተነሣ በራስዋ ስልጣን ሊኖራት ይገባል»*። ተብሏል ፩ኛ ቆሮ 1፩÷፫, ፰-፲ ኤፌ ፭።

ወንድና ሴት አንድ ላይ ይተባበራሉ። ነገር ግን ወንድ የሴት ራስ ነው። በቤት ውስጥ ባል ሚስቱን ራስ የሚያደርጋት ከሆነ የእርሷ ራስ የሆነ ባሏ በሚገኝበት በቤተክርስትያን ጉባዔ ሁሉ እርሷ ራስ መሆን ትችላለች?
ወይም እርሷ÷ባሏን *«አንተ በቤት ውስጥ የእኔ ራስ ነህ»* እኔ ደግሞ በቤተክርስቲያን ወስጥ ላንተ ራስ ነኝ ልትለው ትችላለች? የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እንደራሴ ካህኑ ነውና።

### *2.7 ድንግል ማርያም እና ካህናት*

ሴቶች ካህናት ለመሆን የተጠሩ ቢሆን ኖሮ ድንግል ማርያም በዓለም ውስጥ የመጀመሪያዋ ሴት ካህን በሆነች ነበር። ከቅድስት

ድንግል ማርያም የምትበልጥ ቅድስት ሴት በዓለም የለችምና... ጉዳዩ የይገባኛል ቢሆን ደግሞ ከድንግል ማርያም የበለጠ የሚገባት ሴት የለችም:: ይሁን እንጂ ቅድስት ድንግል ማርያም ካህን ለመሆን አልጠየቀችም:: እርሷ የሁሉም ሐዋርያት መንፈሣዊ እናት ነበረች ነገር ግን ካህን ለመሆን ግን የይገባኛል ጥያቄ አላቀረበችም::

### *2.8 ዲያቆናዊት እና ምስዋዑን ማገልገል*

ይህ ክህነትን ብቻ የሚመለከት አይደለም ነገር ግን የምስዋዑ አገልግሎት የዲያቆን ነው:: ሐዋርያት ሰባት ዲያቆናትን ሲሾሙ ምን ነበር ያሉት? *«ወንድሞች ሆይ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ ለዚህ ጉዳይ እንሾማቸዋለን::»* ነበር ያሉት ሐዋ ፮÷፫

በቤተክርስቲያን ታሪክ ወስጥ ለምስዋዑ አገልግሎት ለትምህርት አገልግሎት ወይም ለግብረገብ ወይም ምስጢራትን ካህናት ለሴቶች ሲፈጽሙ ካህኑን እንዲረዱ ጥቂት ዲያቆናውያት እናገኛለን:: ነገር ግን ምስዋዑን ለማገልገል፣ ቅዱስ ቁርባንን ለማክበር፣ ወይም ለማጥመቅ አልተሾሙም:: ቅዱስ ጳውሎስ በጢሞቴዎስ መልእክቱ በቤተክርስቲያን ሴቶች ወንዶችን እንዲያስተምሩ አልፈቀደላቸውም:: ፪ኛ ጢሞ ፲፩÷፲፪ በኮፕቲክ ቤተክርስቲያንም ሴቶች ሴቶችን ልጃገረዶችን ሕፃናትን እንዲያስተምሩ ይደረጋል እንጂ ወንዶችን አያስተምሩም::

ይቅርታ፤ እኔ ሴቶች ያዘኑ እንዲሆኑ አልፈልግም፤ ነገር ግን ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው:: ይህ ችግርም አይደለም፤ ለተወሰኑ ሰዎች የተወሰነ ጸጋ /ስጦታ/ መስጠቱን ያሳያል እንጂ:: ይህ ሴቶችን መቃወምም አይደለም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ስጦታ የመክፈል ጉዳይ ነው::



እኔ ወደ ሮሜ መልእክት መመለስና ይህን ጉዳይ በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ ምን እንደሚል ማሣየት እፈልጋለሁ:: *«እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንዳካፈለው እንደ ባለአእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ በመካከላችሁ ላለው ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ጸጋ እናገራለሁ:: በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን የብልቶቹም ሥራ አንድ እንዳይደለ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን:: እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን እንደተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገራለን»* ሮሜ ፲፪÷፫-፮:: እያለ ማንኛ ውንም ተልእኮ ወደ መዘርዘር ይሄዳል:: በርግጥ ክህነት አይደለም እንጂ በቤተክርስቲያን ሴቶች ተልዕኮ አላቸው:: ነገር ግን ብዙ ሌላ ዓይነት ኃላፊነቶችና ሥራዎች ናቸው:: ሐዋርያው በመጀመሪያው ጢሞቴዎስ መልዕክቱ *«ሴት በነገር ሁሉ እየተገዛች በዝግታ ትማር ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን አልፈቅድም»* ብሏል ፩ኛ ጢሞ ፪÷፲፩-፲፪:: ያም ማለት በሥርዓተ ቅዳሴም ውስጥ የጸሎቱ ሥራ የካህኑ ነው:: ሴት ግን በዝግታ ትሳተፋለች እንጂ ወንድን ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን አይገባም::

### *2.9 ሴቶችና የክህነት ሥራ /አገልግሎት/*

በክህነት አገልግሎት ውስጥ ለሴቶች የማይመች /የማይስማማ/ ብዙ ነገር አለ:: ለምሳሌም ወንዶችን ማጥመቅ:-

ሴት እንዴት ወንድን ማጥመቅ ትችላለች? ቀላል አይደለም:: ሴት ጳጳስ ብትሆን እና ካህናትን ብትሾም እርሷ የሾመቻቸው ካህናት በሥልጣኗ ሥር፣ በማእረጓ ሥር (በግዛቷ ሥር) የእርሷ የበታቾች



www.ethiopianorthodox.org

ይሆናሉ:: ይህ ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር ይቃረናል::

እርሷ ቅዱሱን ቅባት እንዴት አድርጋ ወንዶችን መቀባት ትችላለች? ሴቶች ወደቤተክርስቲያን መግባት ስለማይችሉበትስ ጊዜ ምን እንበል? ያ ወቅት አገልግሎቷን ለማከናወን ለእርሷ ቀላል አይደለም:: ደግሞ እርሷ ካህን ብትሆንና ለዘጠኝ ወራት ብታረግዝ እንዲሁም በወለደችና ቤት በምትቆይበት በአራስነት ጊዜዋስ? አገልግሎቷ ምን ይሁን? ከዚህ ባለፈ ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ መግባት አልፈልግም:: ነገር ግን በቤተክርስቲያን ውስጥ ከክህነት ውጭ የሆነ ሌላ አገልግሎት በቋሚነት እንዲያገለግሉ የሚያግዟቸው ሴቶችን የሚመለከቱ ብዙ ነጥቦች አሉ::

### *2.10 የቤተክርስቲያን ምስጢራት አገልግሎት የተሰጡት ለወንዶች ነው*

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተክርስቲያንን የምስጢራት አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ለሴቶች የምስጢራትን አገልግሎት አልሰጠም::

ለምሳሌ፡- በዮሐንስ ወንጌል ላይ እንደተገለጸው ጌታችን ክህነትን ሲሰጥ ሥልጣነ ክህነትን የሰጠው ለዐስራ አንዱ ሐዋርያት ብቻ ነው:: *«ኢየሱስም ዳግመኛ ሰላም ለእናንተ ይሁን አብ እንደላከኝ እኔም ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው:: ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ:: ኃጢአታቸአውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው»* ዮሐ ፳÷፳፩-፳፫:: ጌታችን ይህን የሰጠው ለዐስራ አንዱ ሐዋርያት ነው እንጂ ለማንኛዋም ሴት አይደለም::



ምስጢረ ጥምቀትንም በሰጣቸው ጊዜ የማቴዎስ ወንጌልን ብናነብ *«ዐስራ አንዱን ደቀ መዛሙርት ግን ኢየሱስ ወደአዘዛቸው ተራራ ወደ ገሊላ ሄዱ: ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት የተጠራጠሩ ግን ነበሩ:: ኢየሱስ ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዛችኋቸውንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው እነኾም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ»* ማቴ ፳፰÷፲፰-፳ ይላል:: እርሱ የማስተማርንና የማጥመቅን ሥልጣን ለዐስራ አንዱ ሰጣቸው:: ምንም እንኳ ብዙ ሴቶች ቅዱሳት ቢሆኑም፣ እርሱን ቢያገለግሉም፣ እስከ መስቀሉ ቢከተሉትም፣ ክህነትን ግን ለአስራ አንዱ ብቻ ሰጠ:: ሉቃ ፳÷፩፡-፲ ዮሐ ፲፱÷፳፭

ስለ ቅዱስ ቁርባንም ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ *«ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና»* ይላል ፩ኛ ቆሮ ፲፩÷፳፫:: እርሱ ይህን ምስጢር የተቀበለው ከጌታችን ነው:: ይህ ምስጢር ይሁዳ ከተለየ በኋላ ለዐስራ አንዱ ሐዋርያት በጌታችን የተሰጠ ነው:: እርሱም እነርሱን *«ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት . . »* አላቸው እንዲሁም*«. . . ያዘዝኋችሁንም እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው»* ብሏቸዋል:: ይህም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተማሩትን ማለት ነው:: ይህም ደግሞ ለዐስራ አንዱ የተነገረ ነበር:: ጌታችን ከትንሣኤውም በኋላ ለአርባ ቀናት ለዐስራ አንዱ እየተገለጠ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ምስጢር ይነግራቸው ነበር:: የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚመለከት ነገር ሁሉ ይነግራቸው ነበር::

ሴቶች ለእነርሱ በጣም የሚስማማውን ኃላፊነትና አገልግሎት እያከናወኑ በሴትነታቸው ቢኖሩ እንደሚሻል አስባለሁ:: ወፍ በዛፍ

ላይ ሆና አስደሳች ዝማሬን ትዘምራለች፤ በጫካ ውስጥም አንበሳ ያገሣል:: ወፏ አንበሳ ለመሆን ብትፈልግ ተስማሚ አይደለም:: እንደ አንበሳ ከማግሣት ይልቅ ጣፋጩን ዝማሬ በዛፍ ላይ መዘመር ለርግብና ለድንቢጥ (ለወፎች) እጅግ በጣም መልካም ነው:: አንበሳም እንደ ወፍ እዘምራለሁ የሚል ከሆነ ተቀባይነት አይኖረውም::

እንግዲህ ሴቶች ለሴቶች በተሰጠው አገልግሎት ውስጥ ይሁኑ ወንዶችም ለወንዶች በተሰጠው አገልግሎት ውስጥ ይሁኑ::

## *2.11. የሴቶች ኃላፊነቶች*

ሴት ብዙ ኃላፊነቶች አሏት:: ከእነዚህም ኃላፊነቶች ውስጥ ለቤተክርስቲያን አዲስ ትውልድን ማዘጋጀት (መተካት) ለልጆች መንፈሣዊ ክብካቤን መስጠት ነው:: ዋናው ችግር ግን ሴቶች ለልጆቻቸው መንፈሳዊ ክብካቤ የሚያደርጉበት ምንም ሰዓት የላቸውም:: እኔ በታሪክ ውስጥ የምጠቅሳት ቅድስት ሴት አለች፤ እርሷም የሙሴ እናት ዮካቤድ ናት:: በዚህች ቅድስት እናት በተሰጠው ትምህርት ምክንያት ሙሴ ፵ ዓመት እስኪሞላው ብዙ ፈርዖናዊ ጣዖት አምልኮዎች ባሉበት በፈርዖን ቤተመንግሥት ውስጥ ኖረ:: እናቱ በልጅነቱ በውስጡ በተከለችው ሃይማኖታዊ ትምህርት ምክንያት ግን ሙሴ የሃይማኖት ሰው ብቻ ሳይሆን የሃይማኖት ጀግናም ሆነ:: እንዴት? ምክንያቱም በልጅነቱ ቅድስት እናቱ በውስጡ በተከለችው ዕምነትና የሃይማኖት ትምህርት ነው::

ሴቶች ልጆቻቸውን የሚንከባከቡ (በሃይማኖት ትምህርት የሚያሳድጓቸው) ከሆነ ለቤተክርስቲያን ካህናትን (ቀሳውስትን) ያዘጋጁልናል:: በርግጥ የቤተክርስቲያን ካህናት በአንድ ወቅት ልጆች ነበሩ:: እናም ልጆችን እናቶቻቸው የሃይማኖት ትምህርት በደንብ የሚሰጥዋቸው፣ የሚያስረዷቸውና



የሚንከባከቧቸው ከሆነ እናቶች (ሴቶች) በራሳቸው ቀሳውስት ሳይሆኑ ቀሳውስትን ማዘጋጀት ግን ይችላሉ:: በእነርሱ ይከብራሉ፤ ይከበራሉም::

## *2.12. ጥያቄዎች*

ጥያቄ 1.

ሴቶችን ክህነት የሚሾም ጳጳስ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚኖረው በምን ሁኔታ ነው?

መልስ:-

ሴቶችን የሚክን ጳጳስ በእኛ ቤተክርስቲያን የለም:: ሴቶችን የሚክን ጳጳስ በሁሉም ኦርቶዶክሳዊ ቤተክርስቲያን እንደማይኖር አስባለሁ:: ሴቶችን የሚክን ጳጳስ በካቶሊክ ቤተክርስቲያንም ደግሞ እንደሌለ ይሰማኛል:: እኔ ከመጽሐፍ ቅዱስ የምናስተምረውን ብቻ ነው እየተናገርኩ ያለሁት:: ሴቶችን በክህነት መሾም በቤተክርስቲያን ውስጥ መከፋፈልና መለያየትን ለማምጣት ዓይነተኛ ምክንያት መሆኑንም መናገር እፈልጋለሁ:: በጳጳሳትና በቀሳውስት መካከል አለመግባባትን እንጂ ቤተክርስቲያን ሴቶችን ክህነት በመሾሟ የምታገኘው ጥቅም ምንድን ነው? በሌሎች ጳጳሳት የተሾሙትም ወይም የአንግሊካን «ቤተክርስቲያን» በራሷ «ጳጳሳት» የሾመቻቸውን ግብረሰዶማውያን «ካህናት» እና «ካህናት» ሴቶችን ስብከቶች ብዙ አህጉር አንቀበልም ብለዋል::

በጣም በግልጽነት ሌላ መጥቀስ የምፈልገው ነጥብ አለ:: እባካችሁ ይቅርታ አድርጉልኝ እኔ እነዚህን ቃላት ስናገራቸው አዝናለሁ:: ቤተክርስቲያን እንደቀሳውስት ክህነትን ለሴቶች በመስጠት ሴቶችን ልታስደስት ትሞክር ይሆናል? አሁንም እየተከሰተ ያለው ይህ ነው:: ከዚህ በኋላ ለሴቶች ካህናት መሆን ብቻ በቂአቸው



www.ethiopianorthodox.org

አይደለም:: እነርሱ ጳጳሳትም መሆን ይፈልጋሉ:: ጵጵስና ከተሾሙ በኋላ እንኳ ለእነርሱ በቂ አይደለም:: ከዚያም ሴቶች እግዚአብሔር ወንድ ነው ወይስ ሴት ነው? ብለው መጠየቅ ይጀምራሉ::

በርግጥ በመለኮታዊው አምላክ ዘንድ ፆታ የለም:: ነገር ግን እነርሱ ታዲያ «አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር . . .» የምንለው ለምንድን ነው? እያሉ መጠየቅ ይጀምራሉ:: ለምን «እናታችን ሆይ» አላልንም አንልምም? ይላሉ ይህ በብዙዎች የዓለም አብያተ ክስቲያናት ጉባዔዎች ውስጥ ያለ ችግር ነበር:: የተወሰነው ደግሞ «በሰማይ የምትኖሩ ወላጆቻችን ሆይ» እንበል በማለት አስታራቂ ሐሳብ ለማቅረብ ይሞክራል:: ይህ ሐሳብ ግን መጽሐፍ ቅዱስን መለወጥ እንችላለን እንደማለት ነው:: እኛ በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አባት ተብሎ የተጠቀሰባቸውን ቁጥሮች ለይተን ብናወጣ ግን በጣም ብዙ እናገኛለን::

መጽሐፍ ቅዱስን የምንለውጥ ከሆነ በሌላ ሃይማኖቶች የእኛ ክርስትና ምን ይባል ይሆን? እነርሱ ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔር መጽሐፍ አይደለም ሊሉ ይችላሉ:: ማስተካከያ ለማድረግ መሞከር ሊኖርብን ነው:: እነርሱ የሚሏቸው ቃላት ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ የተነገሩ ቃላት አይደሉም::

ጥያቄ 2.

ሴቶች ክህነት እንዲሾሙ የዓለም አብያተክርስቲያናት ሲኖዶስ ይስማማል? ለአንግሊካን ቀሳውስት ሴቶች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ምክር መስጠት ይወዳሉ?

መልስ:-

ይህ እንዳይከሰት እፈልጋለሁ፤ እጸልያለሁም:: እኔ ልለው የምችለው ይህ ነው:: ስለ ቤተክርስቲያን ደኅንነት ምንም ዓይነት



መከፋፈልና መለያየት እንዲኖር አልፈልግምና ይህ እንዳይከሰት እንጸልያለን::

ጥያቄ 3.

በተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ትክክለኛነት ላይ ጥያቄ የሚያነሱ ሰዎች አሉ:: ለዚህ ምላሽዎ ምንድን ነው?

መልስ:-

እኔ በግልጽ ልናገር የምፈልገው የመጽሐፍ ቅዱስ ትችት (critics) ብዙ ጉድለቶች አሉበት:: እስቲ አንድ ምሳሌ ልስጥ:- ይህን የምለው እኛ የምንኖረው በክርስቲያን ሀገር ስላልሆነ ነው:: በዚያም የሆነውን አስገራሚ አጋጣሚ እንደምሳሌ ላንሳላችሁ:: ፕሮፌሰሩ በመንፈሳዊ ኮሌጅ ውስጥ የዮሐንስ ወንጌልን ማስተማር ጀመረ:: ሲያስተምርም «የዮሐንስ ወንጌል ጸሐፊ ማን ነው? ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት አንዱ ነበር ወይስ በ፪ኛ መቶ ክ. ዘመን የኖረ ሌላ ዮሐንስ ነው? በማለት ጠየቀ:: በመጨረሻም የዮሐንስ ወንጌል ጸሐፊ ሌላ ዮሐንስ እንደሆነም ደመደመ:: በዚህም ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ በደቀመዛሙርቱ ወይም በሁለተኛው መቶ ክ. ዘመን በሌሎች ሰዎች ተጽፎ እንደሆነ «እናንተ መጽሐፋችሁን አታውቁትም» ተባልን:: ይህ የትችት መነሻ ሐሳብ ክርስትናን ለመቃወም ጠቅሞአል በብዛትም ታትሞአል::

ለምሳሌም:- ዲዳክትን (Dedacht) ታውቂታላችሁ በክርስቲያን ቀሳውስት ላይ ሰፊ ክርክር /ውይይት/ አድርጎአል:: አብዛኛው የመከራከሪያ ዘዴዎቹ የዚህ ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ትችት ነበር:: ብዙዎቹ ነጥቦች ክርስትናን ለመቃወም ተወስደዋል:: እናንተ

የተወሰነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ተረት ነው የምትሉ ከሆነ ክርስቲያን ያልሆኑት ደግሞ ምናልባት ይህን ነጥብ ወስደው *«መጽሐፍ ቅዱስ አፈ ታሪክ /ተረት/ ለመሆኑ ከክርስቲያን መሪዎች ከካህናቱም ከክርስቲያኖችም ምስክርነት አለን»* ይላሉ::

ወንድሞቼ እነዚህን መጻሕፍት በምታሳትሙ ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጉ:: ለነዚያ ነገሮች የሚኖረውን ምልስት: ጉድለትም (ሐደጋ) በአእምሮአችሁ ውስጥ አኑሩ:: አሁን እነርሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተወሰኑትን መጻሕፍት መንፈሳዊነት ጥያቄ እያደረጉት ነው:: ይህ ማለት ችግሩ ጥርጣሬ ነው:: ምክንያቱም ይህ መንፈሳዊ ነው ወይስ አይደለም የሚል የጥርጣሬ ጉዳይ ነው:: ይህ ደግሞ ከሐዋርያት የተቀበልነው ትውፊት አከራካሪ ሆነ ማለት ነው::

መጽሐፍ ቅዱስን የሚመለከት ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ የተቀበልነው የመጽሐፍ ቅዱስ ትውፊት (ቀኖና) ጥያቄ ውስጥ ገባ ማለትም ነው:: አሁንም ገና አልተቀበሉትም:: ይህ ለአንድ ሕዝብ እምነት መልካም ነው? በሥነመለኮት ደቀመዛሙርት በተወሰነ ትምህርት ተቀባይነት የሚያገኝ ከሆነ ሰዎች ሁሉ የራሳቸውን መጽሐፍ ቅዱስ አጠራጣሪ መጽሐፍ እንደሆነ ማየታቸው ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል? ታዲያ ጥቅሙ ምንድን ነው?

አንድ ጊዜ ተማሪው «እኔ በእምነት ሙሉ ነበርኩ በዚህም ምክንያት ምሁር ለመሆን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ሄድኩኝ ከጥቂት ዓመታት በኋላ እምነቴን አጣሁት:: ምክንያቱም በመንፈሳዊ መንገድ የተቀበልኩት ማንኛውም ነገር ለመቀበልና ላለመቀበል አጠያያቂ ጉዳይ ሆነ:: እናም ምን ተከሰተ? ክርስትና ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው እምነት ሳይሆን የፍልስፍና ዓይነት ሆነ! ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ከጻፈው የመጀመሪያ መልእክቱ ውስጥ ጥቂት ላንብላችሁ አፈልጋለሁ:- «እርሱ ምንም እንኳን በርሱ ዘመን ታላቅ ምሑር



በነበረው በገማልያል እግር ሥር ተቀምጦ የተማረ ታላቅ ምሁር ቢሆንም ምን አለ? « እምነታችሁም በእግዚአብሔር እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም:: በበሰሉት መካከል ግን ጥበብን እንናገራለን:: ነገር ግን የዚህችን ዓለም ጥበብ አይደለም የሚሻሩትንም የዚህችን ዓለም ገዢዎች ጥበብ አይደለም» አለ ፩ኛ ቆሮ ፪÷፬-፮::

በዚሁ ምዕራፍ ቅዱስ ጳውሎስ:- «መንፈሰዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም» ይላል ፩ኛ ቆሮ ፪÷፲፫:: እኛ የመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ለሆነው ለመጽሐፍ ቅዱስ አእምሮአችንን ለማስገዛት ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን ለእኛ አእምሮ ማስገዛት እንሞክራለን:: ታዲያ ከዚህ አልፈን መጽሐፍ ቅዱስን ለመተቸት እንነሳን?

በእርሱ ዘመን ቅዱስ ጳውሎስ በጣም የተማረ ሐዋርያ ነበር:: እርሱ ግን በየዋህነት የመንፈስ ቅዱስን ቃላት ተጠቀመ:: ነገር ግን አሁን እኛ የዓለምን ጥበብ ወይም የሰዎችን ጥበብ ለመጠቀም እንሞክራለን:: ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለን ክብር ምንድን ነው?

በመንፈሳዊ ትምህርቶቻችን ሰዎችን በመጽሐፍ ቅዱስ ትችት ማስጨነቅ? ወይስ የመጽሐፍ ቅዱስን መንፈስ መስጠት ነው ያለብን? መንፈሳዊ ትምህርት (ስነ መለኮት) ፍልስፍና ከሆነ ጥሩ ፍልስፍና አይደለም የጥርጣሬ ፍልስፍና ነው እንጂ:: አንድ ጊዜ አንድ ሰው ወደ ራሱ እያመለከተ *«አዳም ትርፋማ የሚያደርጉትን ብዙ ነገሮች ያውቅ ነበር:: ነገር ግን መልካምና ክፉ ከምታሳውቀው ዛፍ ለመብላት ፈለገ:: ያም የዕውቀት ዛፍ ነበር:: አዳም እንዳበላ የተከሰከሰው*

ፍሬ:: እሱ መልካም ነገርን ብቻ ያውቃል:: ከዚያ በኋላ ግን ክፉ ነገርንም ማወቅ ሁሉንም ነገር መጠራጠርም ጀመረ» አለ::

ጥያቄ 4.

ድንግል ማርያም ኢየሱስ ክርስቶስን በእጇ ይዛዋለች፤ በቅዱስ ቁርባንም ጊዜ ካህኑ ቅዱሱን ሥጋና ክቡሩን ደም በእጆቹ ይወስዳል:: ሴቶች የክርስቶስን ሥጋና ደም በእጃቸው መውሰድ እንዲገባቸው ያልተፈቀደው ለምንድን ነው?

መልስ:-

እኛ ለማኛውም ነገር ተገቢውን ትርጉም መስጠት አለብን:: ክርስቶስ ኢየሱስ የሚገለጥላቸው ቅዱሳን ሴቶች አሉ:: ነገር ግን ይህ ቅዱስ ቁርባን አይደለም:: በእናትነትና በክህነት መካከል ሰፊ ልዩነት አለ:: ድንግል ማርያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በእጆቿ ታቅፋው ነበር ስንል ይህ እናትነቷን ለመግለጽ ነው እንጂ ቅዱስ ቁርባን መያዝዋን አይደለም::

ሴቶች የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም እንዲወስዱ የተፈቀደላቸው በእጃቸው ብቻ አይደለም በአፋቸው በውስጣቸውም ነው::

ደግሞም ድንግል ማርያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በእጆቿ ስታቅፈው የክህነትን ሥራ እየሰራች ነበር? ቅዱስ ቁርባንን መያዟ ነበር? አይደለም:: ሥጋውና ደሙ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም እንደመሆኑ ጉባዔው (ምእመናን) በመላ ይቀበሉታል:: ሴትና ወንድ የሚል ልዩነት የለም:: ልዩነት ሳይኖር ሁሉም ከቅዱስ ቁርባን ይቀበላሉ:: ሥርዓተ ቅዳሴ (Eucharist) ፣ ጽርስፎራው፣ ኅብስቱ፣ ወይኑ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና



ደም እንዲለወጥ የሚጸለይ ጸሎት ነው:: በድንግል ማርያም እንደዚህ ዓይነት ክስተት ግን አልነበረም:: ያ አንድ ሌላ ነገር ነበርና::

ጥያቄ 5.

ቅዱስ ጳውሎስ ሴት ስለወንድ ተፈጠረች እንጂ ወንድ ስለሴት አልተፈጠረምና የሚለውን እንዴት ያብራሩታል?

መልስ:-

ሐዋርያው ስለ ሥነፍጥረት እየተናገረ ነው:: ምክንያቱም ወንድ መጀመሪያ ተፈጥሮአል:: ከዚያም ከእሱ እኩል ረዳቱ ልትሆን ሴት ተፈጠረች:: ሴትና ወንድ በእግዚአብሔር ፊት እኩል ናቸው:: አንድ ሰው ስለፈለገ መጀመሪያ ወይም መጨረሻ መሆን አይችልም:: እያንዳንዱ ሰው መጀመሪያ ወይም መጨረሻ የሚያደርገው ሥራው ነው:: በሥራዎቻቸው በእግዚአብሔር ፊት እኩል ናቸው:: ነገር ግን በሀብታቸው /በጸጋቸው/፣ በኃላፊነታቸው ይለያያሉ:: ወንዶች ልጆች ለምን አንወልድም ብለው ለምን አይጠይቁም? እያንዳንዱ የራሱ ቦታ አለው::

ጥያቄ 6.

ክርስቲያኖች ሁሉ ካህናት ናቸው የሚል ነገር አለ? በሹመት ካህን መሆን ከዚህኛው ክህነት የሚለየው እንዴት ነው?

መልስ:-

በመንፈሳዊው ትርጉም ሁላችንም ካህናት ነን:: ነቢዩ ዳዊት «እጅ መንሳቴም እንደሰርክ መስዋዕት ትሁን» ይላል መዝ ፻፵፥፪:: እርሱም የምስጋና መስዋዕት የመንፈሳዊ መስዋዕት ነው:: ይህ



www.ethiopianorthodox.org

መንፈሳዊው ክህነት ነው እንጂ ምስጢረ ክህነት አይደለም:: «በፊትህ ጸሎቴን እንደ ዕጣን ተቀበለኝ» ይላል መዝ ፻፵፥፪:: ይህ ሥልጣነ ክህነት ነው? ምናልባት ይህ በወንዶች ወይም በሴቶች ሊነገር ይችላል:: ይህ የክህነት መንፈሳዊ ትርጉሙ ነው እንጂ የቤተክርስቲያንን ቅዱሱን ምስጢር የሚያስተዳድርና በምስዋዑ የሚያገለግል ክህነት ትርጉም አይደለም::

ጥያቄ 7.

አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ዕድሜአቸው ከ፲፫ ዓመት በታች ለሆኑ የክርስቲያን ልጆች ቅዱስ ቁርባን መስጠት የለበትም የሚሉት ለምንድን ነው?

መልስ:-

በእኛ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ቁርባንን ለማንኛውም ልጅ እንሰጣለን:: መንፈሳዊ ሕይወትን ከሚጀምርበት ከጥምቀት በኋላም ቅዱስ ሜሮንን እንቀባለን:: በካቶሊክ ቤተክርስቲያንም ይህ እንደሚታወቅ አስባለሁ:: እኛ ከጥምቀት በኋላ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ለልጆች እንሰጣለን::

## *ቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ማን ናቸው?*

ለሰንበት ት/ቤቶች በሚሰጡት ልዩ ትኩረት ይታወቃሉ:: በአገራቸው የሰ/ት/ቤቶች የትምህርት ካሪኩለም በመቅረጽና ለሰ/ት/ቤት መምህራን በመመልመል ያደረጉት አስተዋፅኦ ታሪካቸው በተነሳበት መድረክ ሁሉ ይወሣል:: መንፈሣዊነትን «ሀ» ያሉት በሰ/ት/ቤት ነው:: ሰንበት ት/ቤታቸውን ለ፴፭ ተከታታይ ዓመታት አገልግለዋል:: ኋላ ለጵጵስና መዓረግ ሲደርሱም ለመጀመሪያ ጊዜ የተሾሙት የሰ/ት/ቤቶችንና የቲዮሎጂ ሊቀጳጳስ (የትምህርት ሊቀጳጳስ) ተደርገው ነው:: በተለያዩ ቅጽል ስሞች ይጠራሉ:: «የሕዝብ ሊቀጳጳስ» «ታዋቂው ሊቀጳጳስ» «የ፳ኛው መቶ ክፍለ



ዘመን ዮሐንስ አፈወርቅ (20th centuary Jhon Chrysostom)» ሌላም ...:: በሙስሊሞች ዘንድ እንኳ «የአረቡ አለም ሊቀጳጳስ» በመባል ይጠራሉ የቢኤ ዲግሪ ባለቤት፣ ምሑር ናቸው፤ የትምህርተ ሃይማኖት አስተማሪና አንደበተ ርቱዕ ሰባኪ ናቸው፤ ከ፸ በላይ መጻሕፍት ደራሲ ናቸው፤ የተለያዩ የክብር ዶክትሬት ዲግሪዎችና የአለም አቀፍ ሽልማቶች ባለቤትም ናቸው፤ ግን ደግሞ መናኒ መነኩሴ . . . አቡነ ሺኖዳ ፫ኛ በመንበረ ማርቆስ የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፻፲፯ኛ ፓትርያርክ:: ከሕይወታቸው፣ ከገጠመኞቻቸውና ከትጋታቸው ብዙ እንደምትማሩ እናምናለን:: ሙሉ ታሪካቸውንም እንደሚከተለው አቅርበነዋል::

የተወለዱት አስዩት በሚባል የላይኛው የግብጽ ክፍል ነሐሴ ፫ ፲፱፻፳፫ (ይሔና ከዚህ በኋላ ያሉ አቆጣጠሮች በሙሉ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር ናቸው) የመጀመሪያ መጠሪያ ስማቸው ናስር ጋይድ ነበር:: ናስር ለቤተሰባቸው ከ፭ እህቶቻቸውና ከ፪ ወንድሞቻቸው በመቀጠል የተወለዱ ፰ኛ ና የመጨረሻ ልጅ ናቸው:: እናታቸውን ያጡት በጨቅላነታቸው ነው:: ናስር የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ዳምሃር፣ ባንሃና ኢማን በተባሉ ትምህርት ቤቶች ተማሩ:: በ፲፮ ዓመታቸው ካይሮ ሽብራህ በሚገኝ የቅዱስ እንጦንስ ቤተክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት የቤተክርስቲያን ትምህርታቸውንና አገልግሎታቸውን ጀመሩ:: ቆይተውም የሰንበት ት/ቤቱ መሪ አገልጋይ ሆኑ:: ናስር የተለየዩ ጽሁፎችንና ግጥሞችን በመጻፍ ወደር ያልተገኘላቸው ወጣት ጸሀፊ (Gifted writer) ነበሩ:: በ፲፱፻፵፫ ካይሮ ዩኒቨርስቲ ገብተው በ፲፱፻፵፯ ለአሁኑ ብስለታቸውና አንጋፋ ጸሐፊነታቸው ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው በሚታመነው በታሪክና በእንግሊዝኛ አስተማሪነት በቢኤ ዲግሪ ተመረቁ:: በመጨረሻ መመረቂያ አመታቸውም በአገራቸው ታሪክ የዩኒቨርሲት ተማሪ ሆኖ (ሳይጨርስ) የቲዮሎጂ ኮሌጅ እንዲገባ የተፈቀደለት የመጀመሪያው ተማሪ ሆነው መንፈሳዊ ኮሌጁን ተቀላቀሉ:: በ፲፱፻፵፱ የሰንበት ት/ቤቱን መጽሄት በዋናነት ማዘጋጀት ጀመሩ:: ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርገው ትተው ቅድስት ማርያም ገዳም እስከገቡበት ፲፱፻፶፬ ድረስም በዋና አዘጋጅነት ሰሩ:: በ፲፱፻፶ ከመንፈሳዊ ኮሌጁ በባችለር ኦፍ

ቲዮሎጂ ተመረቁ:: ባስመዘገቡት ከፍተኛ ውጤትም የሐዲስ ኪዳንና የብሉይ ኪዳን አስተማሪ ሆነው እዛው ኮሌጁ ውስጥ ማስተማር ጀመሩ:: በ፲፱፻፶፫ ሔልዋን ወደሚገኘው ሳውርያን የመናንያን የገዳሙ ኮሌጅ ተዛወሩ:: ሐምሌ ፲፰ ፲፱፻፶፬ የወቅቱ የቅድስት ማርያም አበምኔት አባ ቲዮፍሎስ አባ አትናቲዮስ ብለው አመነኰሷቸው:: በገዳሙ ውስጥም የገዳሙን ቤተ መጻሕፍት የማሣደግ ኃላፊነት ተሰጣቸው:: አባ አትናቲዮስ የብቸኝነቱን ሕይወት ይባስ እየሳባቸው ስለመጣ ከገዳሙ ፫ኪ.ሜ ርቆ ከሚገኝ ዋሻ ገቡ:: ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ ፲፱፻፶፫ የአባ አትናቲዮስን የብህትውና ሕይወት ለጊዜውም ቢሆን የሚያስቀር ክስተት የተፈጠረው የወቅቱ የቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕነታቸው አባ ቄርሎስ ፮ኛ አባ አትናትዮስን የግል ጸሐፊያቸው አደረጓቸው:: ከዚያም ከ፫ ዓመታት በኋላ መስከረም ፴ ፲፱፻፷፪ አባ ቄርሎስ አባ አትናትዮስን ሺኖዳ ብለው የጵጵስና መዓረግ ሰጥተው የት/ት (የሰንበት ት/ቤቶችና የቲዮሎጂ ኮሌጅ) ሊቀጳጳስ አድርገው ሾሟቸው:: አቡነ ሺኖዳ በሕይወታቸው አንደዛን ቀን ያለቀሱበትን ቀን አያስታውሱትም:: እንኳን ደስ አለዎት መልእክት ለላኩላቸው ሰዎች ሁሉ የሰጡት ምላሽም በብዙዎች ህሊና እንደታተመ ቀርቷል::

«ለመልእክቶቻችሁ አመሰግናለሁ እንደእውነቱ ከሆነ ግን የእንኳን ደስ ያለህ መልእክት ሳይሆን የጽናቱን ይስጥህ ማስተዛዘኛ ነበረ ለዚህ ጊዜ የሚያስፈልገኝ እንዴት አንድ መነኩሴ ፀጥታውንና ብቸኝነቱን ተነጥቆ ብጥብጥና ሁከት ወዳለባት ከተማ ሲመጣ እንኳን ደስ ያለህ ይባላል? እንዴት ነው ማንስ ቢሆን ማርያምን ቦታዋንና ስራዋን /ጌታ እግር ስር ተቀምጣ መማርን/ ትታ ማርታን ለማገዝ ኩሽና ጉድ ጉድ ስትል እንኳን ደስ አለሽ የሚላት? ለኔ በርግጥም አስፈሪ ነው የሹመቴን ቀን በእንባና በሀዘን አስበዋለሁ:: በእርግጥም የብቸኝነትና የተመስጦ ህይወት ከልኬቶች በላይ ነው:: ከኤጲስ ቆጶስነት ኀረንደውም ከጵጵስና ጋር የሚነፃፀር አይደለም:: እውነተኛው ሹመትና ምርቃት ወዳጆቼ ልብን ለእግዚአብሔር ቤተመቅደስነት ማስመረቅ ነው:: እግዚአብሔር በመጨረሻው ቀን የሚጠይቀን የስልጣን ክህነታችን ደረጃ ሳይሆን የልባችንን ንፅህና ነው::»



በመጋቢት ፱/፲፱፻፸፩ «ዞሮ ዞሮ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከመሬት» እንዲሉ ሥጋ የለበሰ ከሞት አይቀርምና ብፁዕነታቸው አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ወደ ቀደመት አባቶቻቸው ሕብረት ተቀላቀሉ /አረፉ/:: ቅዱስ ሲኖዶስ ቤተክርስቲያኗን የሚመራ ሰው ለመምረጥ ተሰብስቦ ፯ አባቶች ጠቆመ:: ከነሱም ሦስት ብፁዓን አባቶች ብቻ ተመረጡ ከሦስቱ አባቶች አንዱ አቡነ ሺኖዳ ነበሩ::

ጊዜው ጥቅምት ፴ ፲፱፻፸፩ ነው:: ከግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱሳን የአንዱ በዓል ነበር:: ሥርዓተ ቅዳሴው ከጀመሩ በፊት የ፫ቱ ብፁዐን አባቶች ስም የተጻፈባቸው ዕጣዎች ተጠቀለሉና ወደ አንድ ሳጥን (ካርቶን) ተጨመሩ:: ሥርአተ ቅዳሴው እንደተጠናቀቀ ወረቀቶቹ ተፈቱና ሁሉም ሊያያቸው በሚችል መልኩ ከፍ ያለ ጠረጴዛ ላይ ተቀመጡ:: ዓይኖቹ ተጨፍነው የታሰሩ ልጅ ከወረቀቶቹ አንዱን እንዲያነሣ ተዘጋጅቷል የሁሉም ልብ እግዚአብሔር የሚመርጥላቸውን መሪ ለማወቅ በጉጉት ይጠብቃል:: ሕፃኑ አይኑን እንደተሸፈነ እጆቹን ሰደደ:: ካቴድራሉ አንዱ ምዕመን የሚተነፍሰውን ሌላ እስኪሰማ ድረስ ፀጥ ረጭ ብሏል:: የሁሉም ልብ መንፈስ ቅዱስ የሚመርጥላቸውን ቀጣዩን መሪያቸውን ለማወቅ ቆሟል:: ልጁ የሰደደውን እጁን ወረቀት አስይዞ መለሰው . . . በወረቀቱ የተጻፈው ጽሁፍ በቅዳሴው መሪ አባት ተነበበ . . አቡነ ሽኖዳ.... ካቴድራሉ በጩኸት በእልልታና በጭብጨባ ተደባለቀ:: ሁሉም ምዕመን የደስታ እንባ ተራጨ. . .:: ከ፲፬ ቀናት በኋላ ህዳር ፲፬/፲፱፻፸፩ የቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን ደወል ተደወለ:: በዚህም ቀን በበዓለ ሹመታቸው ብዙ ምዕመናን በተገኙበት ተከናወነ:: ብፁዕነታቸው አቡነ ሽኖዳ ፫ኛ መንበረ ማርቆስ የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፻፲፯ኛ ፓትርያርክ... አቡነ ሺኖዳ ለብዙ ወጣቶችና የቤተክርስቲያን አባቶች አርአያ የሚሆኑ በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል:: «የቤተክርስቲያን ዋነኛ ተግባር ለእያንዳንዱ ሰው በቂ እናታዊ ክትትል ማድረግና የድኅነት አገልግሎት መስጠት ነው» የሚሉት አቡነ ሺኖዳ ፴፫ኛ በዓለ ሲመታቸውን ሲያከብሩ

ለተሰበሰቡ ሕዝቦች የግለሰቦችን ህይወትና የታማኝነት አገልግሎትን በተመለከተ እንዲህ ብለው ነበር:-

«ምን ያህሉን ሰው ወደ ንስሓ መራን? አገልግሎት ቃላት /ወሬ/ ወይንም ደሞ እንቅስቃሴ አይደለም፤ አገልግሎት አንዱ ሌላው የሚሰጠው መንፈሳዊነት እንጂ።»

«ወጣቶች የሌላት ቤተክርስቲያን ራእይ የሌላት ነች የሚባል ቀን የሌላት ነገን የማትኖር ቤተክርስቲያን ናት» የሚሉት እኚህ አባት ከዛ በፊት ያልነበረ በ፲፱፻፹ አቡነ ሙሳን የወጣቶች ጳጳስ አድርገው መሾማቸው ለወጣቶች ለሚሰጡት ትኩረት አንዱ እማኝ ነው። አቡነ ሺኖዳ በታታሪነታቸውም ለብዙ ወጣቶች አርአያ የሚሆኑ አባት ናቸው። የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በ፲፱፻፹፩ ከግብጽ ውጪ ፯ የነበሩት ቤተክርስቲያኖቿ ዛሬ ወደ ፪፻ የሚደርሱ ቤተክርስቲያናት ከግብጽ ውጪ አሏት (፹ በአሜሪካ ፴ በአውስትራሊያ ወ.ዘ.ተ)። ከአገር ውጪም ፪ የቲዮሎጂ ኮሌጆች አሏት። ፴፫ የግብጽ ቤተክርስቲያኖች በ፲፪ የአፍሪካ ጉሳዎች (በኬንያ፣ በዛየር፣ በዚምባብዌ፣ ናሚቢያ እና ደቡብ አፍሪካ) ይገኛሉ። ይህም በ፲፱፻፸፮ አባ እንጦንስንና አባ ማርቆስን ወደ አፍሪካ ሀገሮች የመላካቸውና ከ፲ ዓመት በኋላም እራሳቸው የመጎብኘታቸው ውጤት ነው። ኋላም በ፲፱፻፺፰ የተጣራ ወንጌል መልእክት ከግብጽ ውጪ ላሉ ሰዎችም እንዲዳረስ አባ ጳውሎስን የወንጌልና የተልእኮ ሊቀጳጳስ አድርገው ሾሙዋቸዋል። በተጨማሪም የመጀመሪያው የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በደቡብ አሜሪካ ብራዚል፣ ሁለተኛውን ደግሞ በቦሊቪያ አሰሩ።

አብያተ ክርስቲያናት በማሰራት ብቻ ያልተወሰኑት እኚህ አባት በአፍሪካ በአውስትራሊያ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ፰ ገዳማትን መስርተዋል። ከፍተኛ የመጻፍና የማስተማር ጸጋ ያላቸው እኚህ የ፹ ዓመት የእድሜ ባለጸጋ አሁንም በአውስትራሊያ፣ በግብጽና በአሜሪካ በሚገኙ ኮሌጆች በማስተማር ላይ ይገኛሉ። አሁንም የቤተክርስቲያኗ ዋነኛ መጽሔት (አልቃራዝ) ዋና አዘጋጅና በየሳምንቱ የሚታተም ወጣኒ ጋዜጣ ሳምንታዊ



የጽሁፍ አቅራቢ ናቸው ከ፻ በላይ መጻሕፍት በተለያዩ ርእሶች አሳትመዋል። መጻሕፍቶቻቸው በብዛት በሰሚናር ኮሌጅ እና በ፲፱፻፷ዎቹ ካስተማሩት ትምህርት የተወጣጡ ናቸው። ወደ ተለያዩ ቋንቋዎችም ተተርጉመው ብዙ ክርስቲያኖች እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ። በየሳምንቱ ካይሮ፣ በየ፲፭ ቀኑ ደግሞ አሌክሳንደሪያ ቀላልና ማራኪ ቋንቋ በመጠቀም በሚሰጡት ትምህርት ብዙዎችን ከዝለት አድሰዋል፤ ከጥፋት መልሰዋል፤ ከድካም አበርትተዋል፤ አቡነ ሺኖዳ። የተለያዩ አለም አቀፍ ሽልማቶች ባለቤት ናቸው። ከነዚህም መካከል አራት የክብር ዶክትሬቶች (ሶስት ከአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ፩ ከጀርመን ዩኒቨርስቲ)፣ የጽናት ሽልማት ከዩኔስኮ እንዲሁ/ በ፲፱፻፸፰ ክብሮውኒንግ ኢንስቲትዩት የአለም ምርጥ ክርስቲያን ሰባኪነትን ማእረግ አግኝተዋል። አቡነ ሺኖዳ ከዚህ ሁሉ የሥራ ውጥረታቸው ጋር ከሳምንቱ ቀናት ውስጥ ሶስቱን በቅዱስ ቢሾይ ገዳም በብቸኝነት ያሳልፋሉ። ይሄ ገዳም ለአቡነ ሺኖዳ ብዙ ነገር ነው፤ እስኪ አንዱን እናንሣ....

ወቅቱ አቡነ ሺኖዳ በፓትርያርክነት የተሾሙበት ወቅት ነው። አክራሪ ሙስሊሞች በሙሉ ሃይላቸው የግብጽን ክርስቲያኖች ለማጥፋት የሚራወጡበት ወቅት። የወቅቱ የግብጽ ፕሬዝዳንት አንዋር አል ሳዳት ይባላሉ። የክርስቲያኖች ቤት ንብረት ይዘረፋል፤ የክርስቲያኖች ደም እንዲሁ በመና ይፈሣል። ሊቃነ ጳጳሳት ይገደላሉ ወ.ዘ.ተ። ታማኙ ጠባቂ አቡነ ሺኖዳ ስለበጎቻቸው ሲሉ ከመንግስት ጋር መጋጨት ጀመሩ። በመጀመሪያዎቹ አመታት ጤነኛ የነበረው የአል ሳዳትና የብፁዕነታቸው ግንኙነት እየሻከረ መጣ። በዚህ አላበቃም የቤተክርስቲያኗ ልሳን የነበሩት አል-ቃራዝ መፅሔትና ወጣኒ ጋዜጣ ከሕትመት ታገዱ፤ ፰ ሊቃነ ጳጳሳት ፳፬ ካህናት ታሰሩ፤ አባታችንም ወደዚህ ከላይ ወደጠቀስነው ገዳም ተጋዙ። በዚያም ለሦስት ዓመት ተኩል (፵ ወራት) ያህል በግዞት ኖሩ። የሚገርመው ነገር ግን ሳዳት ራሳቸው በነዚሁ አክራሪ ቡድኖች ተገደሉ። በእግራቸውም የአሁኑ የግብጽ ፕሬዝዳንት ሆስኒ ሞባረክ ተተኩ። አቡነ ሺኖዳ ግዞቱን እንደ ጥሩ አጋጣሚ ነበር የተመለከቱት። በነዛ ወቅት ፲፯ [illegible]ሐፎችን ጻፉ። ነገር ግን በውስጥም በወጪም ባሉ ልጆቻቸው ትግል ሆስኒ ሞባረክ አቡነ ሺኖዳን

ከግዞት ለቀቁዋቸው፡፡ በብዙ ጳጳሳት ታጅበው ወደ ቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል (ካይሮ) ሲመለሱ ከ፲ሺህ በላይ ሕዝብ ጳጳሳቸውን ሊቀበሉ ተሰብስበው ነበር፡፡ ሥርዓተ ፀሎቱ ከተፈፀመ በኋላ ያስሙት ንግግር የሚከተለው ነው፡-

«በፍቅር ከተሞሉ ልቦቻችሁ በስተቀር እኔ ማደሪያና መኖሪያ የለኝም፡፡ ከልባችሁ ርቄ አላውቅም፤ ለአይን ጥቅሻ ያህል አንኳ፡፡ በተቻለኝ መጠን እርቀ ሰላምና ፍቅር በቤተክርስቲያንና በመንግስት በቤተክርስቲያኒቱና ሙስሊም ዜጐች መካከል እንዲኖር እጥራለሁ፡፡ ምክንያቱም እኛና እነርሱም ብንሆን አንድ አካል ብልቶች ነን... የግብጽ!»

በአንድ ወቅት የተናገሩትን እናክል፡-

«አንዴ አንድ ሰው በጨዋ አነጋገር ሲመልስልኝ ቅንድቤ ከአይኔ በላይ ነው አለኝ እኔም እንዲህ አልኩት ነገር ግን የአይንህ አገልግሎት ከቅንድበህ ጋር ሊወዳደር በማይቻል መልኩ ይልቃል፡፡ አይንህ የብርሃንህ (የማየትህ) ምንጭ ነው፤ ቅንድብህ ግን ምንም እንኳ ከአይንህ በላይ ቢሆን የጌጥ ያክል ነው ልልህ እደፍራለሁ፡፡ አስኬማህ ከጭንቅላትህ በላይ ነው ሲሉኝ የምሰጠው መልስም ተመሳሳይ ነው፡፡»

የአቡነ ሺኖዳ ታሪክና ገጠመኝ በዚህ ጨረስን፡፡ ወጣቶች ከሕይወታቸው ብዙ እንደምትማሩ ተስፋ እናደርጋለን፡፡

(ኖኅተ ጥበብ ዘደብረ ናዝሬት ልዩ ዕትም መስከረም ፲፱፻፺፮)



www.ethiopianorthodox.org